



ጥላ ግንቦት 2005 ዓ.ም 2ኛ ዓመት ቁ 6 TILA May 2013 2nd Year 6th Edition




## የኢህአዴግ ባለስልጣናትን ዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት የማቅረቡ ጉዳይ ከመለስ ሞት ጋር የሚሞት አይሆንም።

አቶ ኦባንግ ሜቶ የአኢጋን ዋና ስራ አስፈፃሚ




## የኢትዮጵያ ፕሬስ ነፃነት ተምሳሌት ርዕዮት ዓለሙ






---

# "Freedom of expression is one of our most precious rights. It underpins every other freedom and provides a foundation for human dignity. Free, pluralistic and independent media is essential for its exercise."

*UN Secretary-General Ban Ki-moon*
*and UNESCO Director-General Irina Bokova*
*May 3 WORLD PRESS FREEDOM DAY*

# ጥላ

| | |
|---|---|
| **ዋና ስራ አስኪያጅ** | **General Manager** |
| መስፍን አብርሃ | Mesfin Abraha |
| **ዋና አዘጋጆች** | **Editor In Chiefs** |
| እየሩሳሌም ሱሞሮ | Eyerusalem Sumoro |
| ብሩክ ገ/መስቀል(ካርቱኒስት) | Biruk G/Meskel(Cartoonist) |
| ዳዊት ፋንታ | Dawit Fanta |
| **አዘጋጆች** | **Editors** |
| ዮሃንስ ሳምሶን | Yohanes Samson |
| ደበበ ከበደ | Debebe Kebede |
| ፍስሃፅዮን ሃይለገብርኤል | Fisshatsion Hailegeberile |
| **ጽሁፍ አስተባባሪዎች** | **Coordinators** |
| ብርሃኑ ባዩ | Berhanu Baue |
| ኤደን ዳዊት | Eden Dawit |
| አስናቀች ጥላሁን | Asnakch Telahun |
| ህይወት ጥላሁን | Hiwot Tilahun |
| ወልደኪሮስ አስፋው | Weldekiros Asfaw |
| ዮርዳኖስ ሃ/ጊዮርጊስ | Yordanos Hailegiorgis |
| **የኮምፒዩተር ፅሁፍ ቅንብር** | **Computer Graphics** |
| ህሊና ዳዊት | Hilina Dawit |
| ዘውድነሽ ንጋቱ | Zewdinesh Nigatu |


የጥላ መጽሔት አድራሻ/Tila Magazine Address

Mesfin Abraha

Löhrgasse 4

36251 Bad Hersfeld

Email:- tilamagazine@yahoo.de

Web-Site:- tilamagazine.yolasite.com

Tel.No.:- 015222195567,017659384456

017668830082, 017671668780

# ማውጫ


የኢህአዴግ ባለስልጣናትን ....... 7

ሐይማኖት እና መንግስት በኢትዮጵያ 10
የኢትዮጵያውያን መከራ ... 10
ለጥሩ ውጤት ፍቱን ስርዓት 10

የዘር ማፅዳት ዘመቻ 11
መተካካተ ወያኔ 11

ሳንከፋፈል አስከፊውን 12

ካርቱን 13

ተስፋ በወጣቱ 14
ምንያህል መሸከም... 14

ጠላትን ማወቅና... 15

ድምፃችን ይሰማ 16
ከእሾህ የተጠጋ 16
ጉልቻ ቢለዋወጥ 16

ለማን አቤት እንበል? 17
አሁንም አልተሳካም 17
"ጠብ ሲል....ስደፍን" 18
ያልታበሰው የሉሲ እምባ 18

"ግመል ሰርቆ፥ማጎንበስ" 19
በጨለማ ቤት ሠበራ 19

Better to Starve… 21
Still no change 21

EPRDF 22
Enough is enough 22
Anti-terrorism laws… 22

Leave to live 23

Rope to tie... 24
Let`s redeem… 24

Forced Evictions... 25
How long being … 25

Thanks ESAT… 26
Anti-Religious… 26

The Mere… 27
ይሁዳ ሲፈጠር 27

ለ90 ደቂቃ ከአንድ ሚሊዮን ብር /
የአውሮፓ ቻምፒየንስ ሊግን ስታዲየም
ተገኝተው በክብር ለማየት ... 28


## መልካም ንባብ
## ጥላ መጽሔት

# MAY 3 WORLD PRESS FREEDOM DAY

## 2013 Theme: Safe to Speak: Securing Freedom of Expression in All Media

**World Press Freedom Day celebrates its 20th anniversary in 2013. The Day was proclaimed by the UN General Assembly in December 1993, following the recommendation of UNESCO's General Conference. Since then, 3 May, the anniversary of the Declaration of Windhoek is celebrated worldwide as World Press Freedom Day. It is an opportunity to:**

***celebrate the fundamental principles of press freedom;**
***assess the state of press freedom throughout the world;**
***defend the media from attacks on their independence;**
***pay tribute to journalists who have lost their lives in the line of duty. there is a growing awareness that ensure freedom of expression must also necessarily extend to safety online.**

# About Tila

Realizing the fact that the digital age has empowered and made ordinary people across the world irrepressible beyond their imagination, **WE** aims to serve as a credible platform that will spread uncensored interviews, news, commentaries and analyses that are unlikely to see daylight in Ethiopia.

Fortunately, here is where you find **TILA**, the un-disputably best source of information serving the Ethiopian Diaspora community in Europe & America with a proven record of excellence in journalism.

TILA is a political magazine published and distributed by patriotic Ethiopians around Hessen region in Germany. Tila appears in Amharic, English and Germany Languages every 3 months. It is a magazine of quality, responsibility and standard. Entertainment and sport are among our coverage issues next to Ethiopian politics.

As a reader, you are to get useful political and current news in **TILA** than any other publication can offer you. More comprehensive analysis and interpretations than any other media can present to you. In fact, these are some of the qualities of **TILA** that has made it the largest circulating magazine in its category. **TILA** magazine has also partnered with ethiomedia.com, ethiogermany.de, ethiopiazare.com and afroaddis.wordpress.com among others, to deliver reliable and high quality content to our visitors. The articles which are posting here doesn`t represent the Magazine`s Editorial committee, rather the writers.

Don't take the chance of missing this spectacular political magazine. Subscribe to it today! We promise, you won't regret your decision. Reach us on tilamagazine@yahoo.de & tilamagazine.yolasite.com

**Tila Magazine is yours Magazine!**


## ውድ አንባብያን

**ጥላ** መጽሔት በየሶስት ወሩ የሚታተም የፖለቲካ መጹሔት ነው።መጽሔቱ የኢትዮጵያን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ መሰረት አድርጎ በጀርመን አገር የሚታተም ቢሆንም መረጃ መረቦችን በመጠቀም መላውን ዓለም የማዳረስ ዓላማን አንግቦ እየተንቀሳቀሰ ነው።

የአገራችንን ወቅታዊ ሁኔታና ጠቃሚ መረጃዎችን በማካተት ዝናን ያተረፈው የጥምረት መጹሔት አዘጋጆች ያቋቋሙት ጥላ መጽሔት የስሙ ስያሜ እንደሚያመለክተው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ሃይሎች በተበታተነ ሁኔታ የሚያካሂዱትን የትግል ሂደት በማስቀረት በአንድ ጥላ ስር እንዲሰባሰቡ ለማሳሰብና አቅጣጫ ለመጠቆም ነው።

የፖለቲካ ሃይሎች በተበታተነ ትግላቸው ጋት እንኳን መራመድ እንደማይችሉ በመገንዘብ የጋራ ትግል እንዲያካሂዱ ለማበረታታትም ጭምር ነው እ.ኤ.አ ከጥር 2012 ጀምሮ በዚህ ስም መጽሔቱ እንዲጠራ የወሰንነው።በመጽሔቱ አዝናኝና አስተማሪ ዝግጅቶች የሚካተቱበት ሲሆን ስፖርትም ትኩረት ያገኛል። **ጥላ** መጽሔት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሃሳቡን ያለምንም ገደብ በነፃነት የሚያቀርብበት ክፍት መድረክ በመሆኑ በመጽሔቱ የሚወጡት ፅሁፎች በሙሉ የፀሃፊዎቹን እንጂ የጥላ መጽሔት ዝግጅት ክፍልን የማይመለከቱ መሆናቸውንም መግለፅ እንወዳለን።

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት!**



# EDITORIAL



## USA:-We expect a measure beyond annual report!

The United States of America Department of State • Bureau of Democracy, Human Rights and Labor announce Ethiopia´s 2012 Human right 40 Pages Report. The report is trying to cover all kinds of issues and it shows us America`s ears and Noses are very close to Ethiopian people than our own government.

As our understanding, the following phrase has the overall evaluation of Ethiopian government human right records of 2012.

***“The most significant human rights problems included restrictions on freedom of expression and association through politically motivated trials and convictions of opposition political figures, activists, journalists, and bloggers, as well as increased restrictions on print media. In July security forces used force against and arrested Muslims who protested against alleged government interference in religious affairs. Other human rights problems included arbitrary killings; allegations of torture, beating, abuse, and mistreatment of detainees by security forces; reports of harsh and at times life-threatening prison conditions; arbitrary arrest and detention; detention without charge and lengthy pretrial detention; a weak, overburdened judiciary subject to political influence; infringement on citizens’ privacy rights, including illegal searches. And, As of September 2012 there were 70,000-80,000 persons in prison.”***


USA knows very well what should be done beyond the regular declaration of human right reports of countries. Countries like Ethiopia and their people don`t want to hear what the westerns are saying towards their mal-administrations. Rather, the people expect something beyond the report to **re-correct** their government wrong doings.

So, if you (Westerns) are standing for the benefit of the whole Ethiopians or people who are harassed by their own dictatorial rulers, just take a measure than reports . We don`t need to hear such unpractical words. We need now measure measures measure……

**TILA** *Magazine has as usual a special guest of honor and current articles. Have a nice reading.*

### TILA Magazine is yours Magazine!

**TILA is a Multi-lingual Magazine not only you read it, but also you can write on it!**



# ርዕሰ አንቀፅ



# አሜሪካ ፡- ከሪፖርት የዘለለ እርምጃ እንጠብቃለን!

የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዴሞክራሲ የሰብዓዊ መብትና ስራ ቢሮ ሰሞኑን የኢትዮጵያን እ.አ.አ የ2012 የሰብዓዊ መብት አያያዝ 40 ገፅ ሪፖርት ይፋ አድርጓል።ሪፖርቱ ሁሉንም ጉዳዮች ለመዳሰስ ሞክሯል። ሪፖርቱም ያመላከተን የአሜሪካ ጆሮዎችና አፍንጮች ከራሳችን መንግስት በላይ ለኢትዮጵያውያን ቅርብ መሆናቸውን ነው።

እንደ ጥላ መጽሔት ግንዛቤ የሚቀጥለው የሪፖርቱ አካል የ2012ቱን የኢትዮጵያ መንግስት ሰብዓዊ መብት አያያዝ ሪከርድ ሙሉ ግምገማ ያሳየናል ብለን እንገምታለን።

***"ዋነኞቹ የሰብዓዊ መብት ችግሮች ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ገደብ ማለትም፡- ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ያለበት የፖለቲከኞች ጋዜጠኞችና የብሎገሮች እስርና ፍርድ ሲሆኑ በተጨማሪም በህትመት መገናኛ ብዙሓን ላይ ከፍተኛ ክልከላ ይጠቀሳሉ።ባለፈው ሐምሌም የፀጥታ ሃይሎች በሃይማኖት ጉዳይ መንግስት ጣልቃ ገብቷል ብለው ባመኑ የሙስሊም እምነት ተከታዮች ላይ ሃይል ተጠቅመው አስረዋቸዋል። ሌሎች የሰብዓዊ መብት ችግሮች ደግሞ ስውር ግድያዎች ግርፋት ድብደባ የፀጥታ ሃይሎች በእስረኞች ላይ የሚያደርሱት በደል አሰቃቂ የእስር ሁኔታ ህገወጥ ማዋከብና እስር ያለ ክስ ለረጅም ጊዜ ተጠርጣሪዎችን ማጉላላት ደካማና ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ተፅዕኖ ያለበት የፍርድ ሂደት እንዲሁም በግለሰቦች የግል መብቶች ጣልቃ ገብነት ይጠቀሳሉ።እናም እስከ ባለፈው መስከረም ወር ድረስ በኢትዮጵያ ከ70-80 ሺ ዜጎች በእስር ቤቶች እንደሚገኙ ታውቋል።"***

በአገሮች የሰብዓዊ መብት አያያዝ ላይ መደበኛ ሪፖርት በየዓመቱ ከማውጣት ባለፈ መን መደረግ እንዳለበት አሜሪካ በሚገባ ታውቃለች።እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮችና ህዝቦቻቸው በአገራቸው አስተዳደር ችግር ዙሪያ ምዕራባውያን የሚሉትን ነገር ማዳመጥ አይፈልጉም ራሳቸው እየኖሩበት ነውና።ይልቁንም ህዝቦቻቸው ከሪፖርቱ በዘለለ የመንግስታቸውን የተሳሳተ አስተዳደር ለማስተካከል ከአሜሪካ መንግስት አንድ ነገር ይጠብቃሉ።

ስለዚህ ምዕራባው ን ሆይ ለመላው ኢትዮጵያውያንና በአምባገነን መንግስቶቻቸው በደል ለሚደርስባቸው ህዝቦች ጥቅም የቆማችሁ ከሆነ ከሪፖርት የዘለለ እርምጃ ውሰዱ።ተግባራዊ የማይሆኑ ቃላቶችን መስማት አንፈልግም።አሁን የምንፈልገው እርምጃ እርምጃ እርምጃ ነው።

**ጥላ** መፅሄት የዚህ እትም ልዩ እንግዳና የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑትን አቶ ኦባንግ ሜቶን በመጋበዝ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ አወያይታለች።ወቅታዊ ጉዳዮችም ተካተዋል። መልካም ንባብ ምኞታችን ነው:: አብረን እንዝለቅ!

**ጥላ መጽሔት የእናንተው መጽሔት ናት! "ጥላ የሚያነቧት ብቻ ሳትሆን የሚፅፉባትም መጽሔት ናት"**




"It's injustice that motivates us to do something, to take risks, knowing that if we don't, things will remain the same".

Digna Ochoa (1964-2001)




**Digna Ochoa was a human rights lawyer in Mexico. She was born May 15, 1964 in Misantla, the state of Veracruz. Assassinated: October 19, 2001**

# <u>እኛ ስንስተካከል ዓለምና የፍርድ ሚዛንዋ ወደ እኛ ያዘማሉ።</u>

# የኢህአዴግ ባለስልጣናትን ዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት የማቅረቡ ጉዳይ ከመለስ ሞት ጋር የሚሞት አይሆንም።

## አቶ አባንግ ሜቶ የአኢጋን ዋና ስራ አስፈፃሚ

አቶ አባንግ ሜቶ ይባላሉ።የስቃይ ሰለባ የሆኑና እሳቸው የሚመሩትን ድርጅት ድጋፍ ያገኙ ኢትዮጵያውያን "አባታችን" ይሏቸዋል። እሳቸው ብዙ ሃላፊነት ያለባቸው ሰው በመሆናቸው ዛሬ አፍሪካ ነገ አውሮፓ ከነገወዲያ አሜሪካ ከዛም ኤሺያ የማይዞሩበት ዓለም የለም።ግን የትም ይሂዱ ሁል ጊዜም በራቸው ለሁሉም ዜጋ ክፍት ነው።የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ወይም አክቲቪስት ናቸው።አሁን አሁን በየትኛውም ዓለም ኢትዮጵያን አስመልክቶ በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ ግንባር ቀደም ተጋባዥ በመሆን የሚያምኑበትንና ለአገሪቱ ይጠቅማል የሚሉትን ሃሳብ ግራና ቀኝ ሳያዩ በቅንነትና በግልፅ ያቀርባሉ።በዚህ አቋማቸውም የበርካቶችን ቀልብ ለመግዛት ችለዋል እንደበተ-ርቱዕ ናቸውም ይሏቸዋል በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎች- አቶ አባንግን።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አባንግ ስም ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች በማይተናነስ እንዲያውም በሚልቅ ሁኔታ ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ያላቸው ሰው በመሆናቸው የኢትዮጵያውያንን ብሶትና ቅሬታ በማንኛውም መድረክ ላይ ፊት ለፊት በማቅረብ ለመፍትሄ የሚሰሩ ናቸው። ምንም እንኳን እንዲህ ይሰራል መባላቸውን ውዳሴ ከንቱ አታድርጉብኝ ቢሉም እውነታውን ግን ከመግለፅ ወደ ሁዋላ ለማለት ያስቸግራል።

የጥላ መጽሔት የዚህ እትም ልዩ እንግዳ የሆኑትን አቶ አባንግን በተለያዩ ወቅታዊና አንገብጋቢ የአገራችን ጉዳዮች ዙሪያ ጋዜጠኛ መስፍን አብርሃ ከሚኖሩበት ከካናዳ አነጋግሯቸዋል።መልካም ንባብ።

**ጥላ፡-** ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) መቼ ተቋቋመ? ለምን ተቋቋመ? ዓላማውስ ምንድን ነው?

**አቶ አባንግ ፡–** ሰዎች ነን። በሰውነታችን ማሰብና ማከናወን የሚገባን አቢይ ጉዳይ ቢኖር በተፈጠርንበት ደረጃ ልናስብ ይገባል። በጎሳና በዘር በማሰብና በመደራጀት ላለፉት አርባ ዓመታት የፈየድነው ነገር የለም። የጎሳ አደረጃጀት ተከትለን ምንም ያተረፍነው ነገር እንደሌለ ኢትዮጵያዊያን ነጋሪ የሚያስፈልጋቸው አይመስለኝም። ገዢ ነን የሚሉትን ጨምሮ ሁላችንንም ነጻ የሚያወጣ ህብረት ያስፈልጋል። የጋራ ንቅናቄያችን ይህንን ሃላፊነት ወስዶ የተመሰረተ የበጎ ፈቃደኞች ስብስብ ነው። የተቋቋመው በነሐሴ ወር 2000 ወይም ኦገስት 2008 ዓ ም ነው።

**ጥላ፡-** አኢጋን የሚንቀሳቀስባቸው አገሮች የት የት ናቸው?ተቀባይነቱስ ምን ያህል ነው?

**አቶ አባንግ ፡-** አኢጋን ድንበርና አገር የለውም። የድርጅታችን ዋናው መቀመጫ ንጹህና የሰውነት ደረጃውን አውቆ፣ ወይም ለማወቅና በዛው ደረጃው በማሰብ በሚስማሙ ወገኖች ልቡና ውስጥ ነው። ስለዚህ በሁሉም ቦታ አለን ማለት ነው። ድርጅታችንን መስርተን ወደ እንቅስቃሴ ስንገባ ዓላማችንን መዝራት ጀመርን። አሁን በቁጥር የማንገልጻቸው ለዓላማችን እየተገዙ ነው። ምርቱን በመሰብሰብ ላይ ነን። በተለያዩ መድረኮች የአኢጋን መርህ እየተሰበከ ነው "ሁላችም ነጻ ካልወጣን ማንም ነጻ ሊወጣ አይችልም" በሚል መሪ ቃል የመመራትና አቋምን የማስተካከል ዝንባሌ ባደባባይ እየሰማን ነው። ይህ ታላቁ ስኬታችን ነው።

**ጥላ፡-** "ሁላችንም ነፃ ካልወጣን ማንም ብቻውን ነፃ ሊሆን አይችልም" የሚል መፈክር ያነገባችሁት ለምንድን ነው?ከማ ነው ነፃ የምንወጣው?እንዴትስ ነው ነፃ መውጣት የሚቻለው?

**አቶ አባንግ ፡-** መፈክራችን መቅደም ያለበትን የሚያመለክት ነው። ለሰው ልጅ ቀዳሚው ነገር በሰውነት ደረጃ ማሰብ መቻሉ ነው። ሰዎች በተፈጠሩበት ውድ ስብዕናቸው ሊኖሩና በዛው መጠን ሊያስቡ ይገባል። ከጎሳቸውና ከዘራቸው በላይ ሰውነታቸው ወይም ሰው መሆናቸው ትልቅ ነገር ነው። ሁሉም ነገር ከሰውነታቸው በታች ነው። ለምሳሌ አንድ መኪና ለገዛ ሰው መኪናው የሱ ለመሆኗ በሱ ስም የተዘጋጀ የባለቤትነት መታወቂያ ይሰጠዋል። የመኪናዋ ባለቤት እሱ በመሆኑ መኪናዋ "የአቶ እገሌ መኪና" ተብላ ትጠራለች። ይህ ትክክለኛው አግባብ ነው። ማንም ሰው በገዛው መኪና




አይጠራም። መኪናዋ የባለቤቷ መጠሪያ ወይም የገዛት ሰው የበላይ አትሆንም። ስለዚህ ከትልቁ ነገር ይልቅ ትንሹን ነገር መምረጥ ትክክለኛ አይሆንም። መቅደም ያለበት ሰውነት ወይም ሰው መሆን ነው የምንለው ለዚህ ነው። ሰውነትን አስቀድሞ በሰውነት ደረጃ ማሰብ ትልቅነትም ነው። በሰው ደረጃ ተመጥኖ ማሰብ ከሌሎቹ ካልጠቀሙን አስተሳሰቦች ሁሉ የበላይ ስለመሆናችን ማረጋገጫ ይሆናል።

**ጥላ፡-** ሰብዓዊነት ከምንም ነገር ጋር ሊወዳደር የሚችል ጉዳይ አይደለም።ጎሳ የሚለው አባባል በስህተት ወይም በግድ ጎሰኝነቱን የተቀላቀሉትን ወገኖች አያስኮርፍም ወይ?ድርጅታችሁ የመላው ኢትዮጵያዊ ድርጅት እንደመሆኑ እነዚህን ወገኖች አስተሳሰባቸውን እንዲያስተካክሉ በማድረግ አኢጋንን እንዲደግፉ ማድረግ አይቻልም ነበር?

**አቶ አባንግ ፡-** አስቀድሜ የገለጽኩት ይመስለኛል። በጎሳ ተደራጅተን ምን አተረፍን? በጎሳ ተቧድነን ምን አተረፍን? በጎሳና በዘር ተሰባስበን ምን ተጠቀምን? ለዚህ ጥያቄ መልስ መስጠት የሚችሉ በርካታ ወገኖች አሉ። ውጤቱ በደንብ የታየና ሊካሄድ በማይችል ደረጃ ማስረጃ የሚቀርብበት ነው። እንግዲህ ከዚህ ውጤት አልባ የድርጅት አዙሪት እንውጣ ማለት ምን ክፋት አለው? ለምንስ ቅሬታ ይፈጥራል? በሰውነት ደረጃ በማሰብ፣ ሰብአዊነትን በማስቀደም ብንሰባሰብ ቢያንስ ራሳችን በራሳችን ወገን ላይ የምንፈጽመውን በደልና ግፍ እናቆማለን።

የርስ በርስ መከባበርና ተረዳድቶ መኖርን በተፈጠርንበት ውድ ደረጃችን ጋር በማጣጣም ካከናወነው እናተርፋለን። ስለዚህ ከጎሰኛነት አስተሳሰብ መላቀቅ ግድ ነው። ወደ ሰውነት መሸጋገር!!

**ጥላ፡-** "ቅድሚያ ለሰብዓዊነት" ብቻ ቢባል ሁሉንም ያሳትፋል።የተሳሳተውንም ያርማል ብለን እንደ ጥላ መጽሄት እናምናለን።ምን አስተያየት አሎት?



አቶ ኦባንግ፡- ትክክል ናችሁ ብዬ አምናለሁ። ከናንተና እናንተን ከመሳሰሉ የሚዲያ አካልትም ብዙ ስራ ይጠበቃል። አገርን ማዳን የሁሉም ሃላፊነት እንደሆነ ያለ አንዳች ወገናዊነት አምኖ ማሳመን የሚዲያው ፈንታ ነው።

**ጥላ፡-** እስራኤልና ኖርዌይ የሚገኙ ስደተኛ ኢትዮጵያውያንን ከችግር ለማላቀቅ ያከናወናችሁዋቸው ተግባራት ምን ውጤት አስገኙ?ኢትዮጵያውያኑንስ በአስገዳጅ ወደ አገራቸው ከመመለስ ታደጋችሁዋቸው ወይ?

**አቶ ኦባንግ፡-** ከዚህ ቀደም ጎልጉል በሚባል የድረ ገጽ ጋዜጣ ላይ በዝርዝር ተናግሬያለሁ። የአኢጋን ቤተሰቦች በዚህ ረገድ ብዙ ሰርተናል። በየጊዜው የሰራነውን ብንናገር ሚዲያ ማጨናነቅ ይሆናል። እኛም አንፈልገውም። ይህንን ስል ግን በቂ ስራ ሰርተናል ለማለት አልደፍርም። ውስን አቅም ቢኖረንም ከችግሩ አንጻር መስራት የሚገባንን ያህል አልሰራንም። አንድ መታወቅ ያለበት እውነት አለ። ስራው አድካሚና በርካታ ደጆችን ማንኳኳት የሚጠይቅ ነው። በተጠቀሱት አገሮች የሚኖሩትን ወገኖች ጉዳይ ለአፍታም የምንዘነጋው አይደለም። ከተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና ተጽዕኖ ፈጣሪ አካላት ጋር እየሰራን ነው። መፍትሄም ያገኙ ወገኖች አሉ። በዋናነት ግን መታሰብ ያለበት ነገር የስደት ፈቃድ ስለማግኘት ሳይሆን አገራችን ላይ ተከብረን የምንኖርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው። ሁሉም እልህ አስጨራሽ ትግል ይጠይቃል።

**ጥላ፡-** በኬንያና በአውሮፓዊቷ ማልታም በስደት የሚሰቃዩና ለእስር የተዳረጉ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንዳሉ መረጃዎች ይጠቁማሉ።እነዚህን ወገኖቻችንን ከስቃይ ለመታደግ ምን የታሰበ ነገር አለ?

**አቶ ኦባንግ፡-** ተመሳሳይ ጉዳይ ነው። በተመሳሳይ እየሰራንበት ነው። ለጊዜው ቁጥራቸውን በውል የማላውቃቸው ሰዎች ነጻ እንዲሆኑ አድርገናል።

**ጥላ፡-** ከስደት ውጪ በስራ ምክንያት ከአገር ወጥተው በተለያዩ አረብ አገራት አሳሪ መከራቸውን እያዩ የሚገኙትን እህቶቻችንን እንባ ለማበስ አኢጋን ምን አስቧል?በተለይ እርሶ ያሎትን ዓለምአቀፍ ተቀባይነት ተጠቅመው ምን ለማድረግ ተዘጋጅተዋል?

**አቶ ኦባንግ ፡-** እጅግ ረፍት የሚነሳ ጉዳይ ነው። አንድ አገር እመራለሁ የሚል መንግስት ዜጎቹን መጠበቅና መብታቸውን ማስከበር ሲያቅተው መመልከት ያሳዝናል። አንድ ዜጋ አድኑኝ ብላ ኤምባሲ በር ላይ ስትደርስ በር ዘግቶ ጀርባ መስጠት በየትኛውም መስፈርት የሰውነት ደረጃንና ሰው የመሆንን መስፈርት ያጎድለዋል። በዚህ በኩል ያለው ችግር ስፍር ቁጥር የለውም። አስቀድሜ እንደገለጽኩት የበኩላችንን እያደረግን ነው። ችግር አለ በተባለበት ቦታ ሁሉ ለመድረስ እንጥራለን። በዚህም መላው የአኢጋን ቤተሰቦች ደስተኞች ናቸው። ለጊዜው በዝርዝር መግለጽ ባልችልም ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ማህበራት ጋር እንዲሁም ሴቶች ጉዳይን በሃላፊነት ለመከታተል በቅርቡ ከተቋቋሙ እህቶቻችን ጋር ለመስራት ሃሳብ አለን። ጅማሬው ጥሩ ይመስላል።

**ጥላ፡-** አገሪቱ ውስጥ ያሉትን ችግሮች ለማስረዳት በበርካታ መድረኮች ተገኝተው ከፍተኛ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ ይታወቃል።በጀርመንም የ2012 ምርጥ ሰው ተደርገው ተመርጠዋል።ጥረቶ ምን ውጤት እያመጣ ይገኛል?

**አቶ ኦባንግ፡-** በደፈናው ምርጥ ሰው ነኝ ብዬ አስቤ አላውቅም። እኔ የምመራው ድርጅት ዓላማና መርህ ግን አማራጭ የሌለው መንገድ በመሆኑ "የተመረጠ" መርህ እንደሆነ አምናለሁ። ክብሩና ምርጥነቱ የመነጨው ወይም መነሻው የድርጅቱ ዓላማ ከሆነ ደስታው ለመላው የአኢጋን ቤተሰቦችና የዓላማው አፍቃሪዎች በመሆኑ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እወዳለሁ። ለአገራችን የተወሳሰበ ችግር መፍትሄ ነው ለምንለው መርህ ለተሰጠው ክብር ደግሞ መራጮቹን አመሰግናለሁ። ከዚህ በተለየ የምለው የለም። ሃሳቡን ያመጡትና ከድምዳሜ የደረሱት ወገኖች ቢጠየቁና ምላሻቸውን ቢሰጡ የተሻለ ይሆናል። በግሌ አንድ የማልስማማበት ጉዳይ አለ። እኔ አንድ ግለሰብ ነኝ። ደጋግሜ ቤተሰብ እያልኩ የምጠራው የአኢጋን ስራ አመራር ከሚወስነውና ከሚያወጣው መርሃ ግብር ውጪ በግሌ የማደርገው ነገር የለም። ግለሰብ ላይ የተንጠለጠለን ሙገሳና ውዳሴ ብዙም አልወደውም። አስቦ፣ አልሞ፣ መዝኖና ፣በሰከነ አእምሮ መርምሮ መራመድ ያስደስተኛል። ከምንም በላይ ምክንያታዊ መሆን የተፈጠርንበት ደረጃ መለኪያ እንደሆነ ይሰማኛል። አኢጋን ውስጥ እንዲህ ያለው አስተሳሰብ የተለመደ ነው።

**ጥላ፡-** የኢህአዴግ ከፍተኛ አመራሮችን በጦር ወንጀለኝነት ለመክሰስ የሚያስችል ማስረጃ/መረጃ አቅርባችሁዋል።ግን እስካሁን ያየነው ነገር የለም።ምክንያቱ ምንድን ነው?ያቀረባችሁዋቸው መረጃዎች ማስረጃ መሆን አልቻሉም ወይስ ሌላ ችግር አለ?

**አቶ ኦባንግ፡-** በችኮላና እኛ በምንፈልገው ፍጥነት የሚሆን ነገር የለም። ስንቸኩል የያዝነውንም እናጣለን። ኢህአዴግንና ተባባሪዎቹን በፈጸሙት ወንጀል መነሻ ከሶ ለፍርድ እንዲቀርቡ ለማድረግ የመረጃ ችግር የለብንም። አንድ ምሳሌ ላንሳ። የሱዳን ፕሬዚዳንት አልበሽር በጦር ወንጀለኛነት እስር ተፈርዶባቸዋል። እስካሁን ግን ያሰራቸው የለም። ብዙ የተወሳሰቡ ጉዳዮች አሉ። ብዙ ጉዳዮች በጊዜ ምላሽ ያገኛሉ። አቶ መለስን በዓለም አቀፉ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት ከሰናል። ፋይላቸው ተከፍቶ እንዲከሰሱ ከውሳኔ ተደርሶ ነበር። በመካከሉ ሞቱ። ከሞት ቀስቅሰን የክሱ ሂደት ይቀጥል ማለት ራሱን የቻለ ሌላ ጉዳይ ነው። አሁን በስልጣን ላይ ያሉት ታዛዦችም መከሰስ አለባቸው። መለስ ቢሞቱ የተቀሩት አሉ። ጉዳዩን ወደዛ ቀይረን እየሰራን ነው። አሁን በዝርዝር ለመናገር ቢችግረኝም አሁን በስልጣን ላይ ያሉትን ወንጀለኞች ህግ ፊት ለማቅረብ የመረጃ ችግር እንደሌለ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ። እንዳልኩት ጊዜ የሚወስድ ሥራ ነው፡፡

**ጥላ፡-** በአንፃሩ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት በቅርቡ ኢህአዴግ የሚመራት ኢትዮጵያን በአመራር ቦታ እንድትገባ መርጧታል።አለ የምንለው ችግር በእውነት ስለሌለ ነው

ወይስ እኛ አለ የምንለውን ችግር ማሳየት ስላቃተን ነው?

**አቶ አባንግ፡-** አየህ ልዩነታችን እዚህ ላይ ነው። እነሱ ላመኑበት ዓላማ ሌት ተቀን ይሰራሉ። እኛ ገና ከራሳችን ጋር አልታረቅንም። እንደውም የነሱን የጎሳና የብሄር አዝማች እያስተጋባን ራሳችንን ለበለጠ ሽንፈትና ለተስፋ መቁረጥ እናመቻቻለን። እነሱ የህልውና ጉዳይ ብለው ሃይላቸውን አስተባብረው ይታገላሉ። እኛ በተቃራኒው እንባላለን፤ እርስበርስ እንጣላለን። ለምንና እንዴት እንደምንደራጅ እንኳ በወጉ ያልተረዳን አለን። አሁን ለመቀየር የተነሳነው እንዲህ ያለውን አክሳሪ አስተሳሰብ ነው። ከስሜት የጸዳ አስተዋይነት የተሞላው ትግል ማካሄድ ግድ ነው። መስፈሪያችንን ማወቅ አማራጭ የለውም። እኛ ስንስተካከል ዓለምና የፍርድ ሚዛንዋ ወደ እኛ ያዘማሉ። የዚያኔ የተባበሩት መንግስታትም ሆነ የፍትህ አካሎችና ፍትህ አቀናባሪዎች አንቀጽ ይጠቅሱልናል። አሁን በርካታ ጉዳዮች አፋፍ ላይ ናቸው። ተጠናክሮ መቀጠል ነው።

**ጥላ፡-** በኢህአዴግ መራሹ መንግስት ተጠንስሶ እንደ እናንተ አይነት መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን አስመልክቶ በወጣው ሕግ ላይ ድርጅታችሁ ምን አስተያየት አለው?

**አቶ አባንግ፡-** ይህ ብዙ የተባለለት ጉዳይ ነው። እኛም አቋማችንን አሳውቀናል።ኢህአዴግ ህግ እየጠቀሰ ዜጎችን ማፈን ልዩ ባህሪው ነው። እንደፈለገው የሚተረጉመው ህግ በማውጣት፣ እንዳሻው የሚፈርዱለት ፈራጆች በማሰማራት ህግን ከፊት አድርጎ ዜጎችን፣ ማህበራትን፣ ድርጅቶችን፣ ሲቪክ ተቋማትን፣ ባለሙያዎችን፣ አገራቸውን የሚወዱትን....... ወህኒ ወርውሯል። እየወረወረ ነው። የአገዛዙ አንዱና ከፉ መገለጫው እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

**ጥላ፡-** የእናንተን አይነት ድርጅቶች እንቅስቃሴ ለማስተዋወቅና ገለልተኛ የሲቪክ ማህበራት እንዲጠናከሩ ለማስቻል ከነፃው ፕሬስ ምን ይጠበቃል?

**አቶ አባንግ፡-** አሁን ያሉት ሚዲያዎች አገዛዙን በተለያየ መንገድ ለሚቃወሙ ድርጅቶችና ፓርቲዎች ብሎም ግለሰቦች በመወገን የሚዘግቡ ናቸው። ሚዲያዎቹ መረጃ ከማስተላለፍ ጀምሮ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እጅግ ዋጋ ያለው እንደሆነ ይሰማኛል። እንደ ድርጅታችን እምነት ከሆነ ሚዲያዎች አሁን ካላቸው አስተዋጽኦ በላይ ማደግ ይገባቸዋል። የመስማማት አቋም በማራመድ ብቻ አገርና ህዝብን መጥቀም አይቻልም። የተቃዋሚ ፓርቲ




መሪዎችን መሞገት አለባቸው። መከራከርና መመርመር አለባቸው። የተቃዋሚ ፓርቲዎችን መገሰጽ አለባቸው። መፈታተን አለባቸው። መከራከርና መመርመር አለባቸው። ጋዜጠኛነት ሙያው እንደሚያዘው የመስማማትና የመቀበል ጉዳይ አይደለም። ለምሳሌ እኔን አንድም ጊዜ አንድም ሚዲያ ተከራክሮ ጠይቆኝ አያውቅም። ለምን? ወርቅ በእሳት እንደሚፈተነው ሁሉ በተለያዩ ደረጃዎች የምንገኝ አካላት አንዳንዴ እንኳ ቢሆን ልንፈተን ይገባልና ሚዲያዎች ከዚህ አንጻር የጋዜጠኛ ስራ ስለመስራታቸው ራሳቸውን ሊመረምሩ ይገባል።

**ጥላ፡-** በቅርቡ የመሬት ነጠቃን አስመልክቶ በዩኤስ ኮንግረስ ላይ ባልተለመደ ሁኔታ ሃይለቃል መጠቀምዎ ተሰምቷል።ለምን?

**አቶ አባንግ፡-** በፍጹም። የመከራከሪያዬን ሃሳብ ከተከራካሪው ሰው ከፍ በማድረግ መናገሬን አስታውሳለሁ።

**ጥላ፡-** ስለመሬት ነጠቃ እርስዎ ያቀረቡትን ጉዳይ የተቃወሙት የህወሃት ሰው ናቸው?

**አቶ አባንግ፡-** ነገሩ እንዲህ ነው። በዩኤስ ኮንግረንስ ስለ መሬት ነጠቃ ያቀረብኩትን ንግግር አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ኤምባሲ የመጡ አንድ የአገዛዙ ሰው "የምታወሩት ሁሉ ውሸት ነው። ሰዎችን ወደ ስህተት ጎዳና እየመራችሁ ነው" በማለት ሃቀኛ ለመሆን ሞክረው ተናገሩ። እኔ መልስ የመስጠት እድል አገኘሁና ባለስልጣኑ ሊያስተባብሉ በማይችሉበት ሁኔታ መለስኩላቸው። የምንናገረው እውነት እንደሆነ አስረግጬ አስረዳሁ። የመከራከሪያዬን ጭብጥ ሰውየው ከተናገሩበት ደረጃ በማሳደግ ከፉ ቃል ሳልጠቀም እሳቸውን ጭምር ነጻ ለማውጣት እንደምንሰራ ነገርኩዋቸው። ይኸው ነው። ዘለፋ የለም። ዘለፋ አልወድም። በመዛለፍ አላምንም። የምትናገረው ነገር ማሳመኛ ነጥብ አለውና የገዘፈ መሟገቻ ከታከለበት በንግግሩ ውስጥ ያለው የእውነት ሃይል ከስድብ በላይ ሊሆን ይችላል። እነሱ ቢጠሉንም እኛ ግን ከቂምና ከበቀል ርቀን እነሱን ነጻ እስከማውጣት ድረስ እንደምናስብ ስንነግራቸው ይዞርባቸዋል። እውነት መሆኑን ለመቀበል ያዳግታቸዋል። የኖሩበት የፖለቲካ ሰፈር፣ ያደጉበት የመተላለቅ መንገድና የተመረቁበት የጭካኔ መንፈስ ይህን አይነቱን ለሰብአዊነት ቅድሚያ የሰጠ የመረዳዳትና ራስን ከፍ አድርጎ በእኩልነት የማኖር ስርዓት ስለማያውቁ ግራ ይጋባሉ። ማስተማርና ሰዎችን ወደ ሰውነት ደረጃ ከፍ ማድረግ አድካሚ ስራ ነው የምለው ለዚህ ነው።

**ጥላ፡-** እና ሃይለ ቃል ጠቃሚ አይደለም እያሉ ነው?

**አቶ አባንግ፡-** አዎ! ምን ያደርጋል። እንግሊዞች "**use soft words and hard argument**" የሚሉት አባባል አለቸው። በጨዋ ቋንቋ ጠንካራ መከራከሪያ በማቅረብ መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል። ዘለፋ ከሰውነት ደረጃ የመውረድ ያህል ይሆንብኛል። እኔ ጠላት አለኝ ብዬ አላስብም። የቆምንበት ኣላማም ለዘለፋ እውቅና አይሰጥም። በዘለፋ ለውጥ ማምጣትና ማሸነፍ አይቻልም።

**ጥላ፡-** አቶ አባንግ ለፍፁም ቅንነቶና ተባባሪነቶ የጥላ መጽሄት ዝግጅት ክፍል ላቅ ያለ ምስጋናውን ያቀርባል።

**አቶ አባንግ፡-** እኔም ለተሰጠኝ ዕድል ከልቤ አመሰግናለሁ፡፡

# ሐይማኖት እና መንግስት በኢትዮጵያ

**Yeshi Gete/Zeil**

ኢትዮጵያ አገራችን ከጥንት ጀምሮ ባለታሪክና ህዝቦቿም ተከባብረው በአንድ ጥላ ስር ሆነው የሚኖሩባት ለሌሎች አገራት የመቻቻልና አብሮ የመኖር ዘዴ ያሳየች አገር በቀደምት ገዥዎች ላይ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ወያኔዎች ጣልቃ መግባት ከጀመሩ ሰነበቱ።

አሁን ደግሞ ስር እየሰደደ የመጣው የወያኔ መንግስት ዜጎችን ማገንላታቱ ሳያንሰው አሁን ደግሞ በሃይማኖት ጣልቃ እየገባ ነው።እንደሚታወቀው ውድ የእናት አገራችን ዜጎች ማለት ክርስቲያኑ እና ሙስሊሙ ተከባብሮ እና ተፈቃቅሮ እንደሚኖር አለም ይመሰክራል።ነገር ግን ሰላምን የማይወደው የወያኔ መንግስት የክርስቲያኑን ገዳማት ተደፍሮ ተነክቶ የማያውቀውን ገዳማት መሬታቸውን እየነጠቀ ገዳማትን እያፈረሰ ለሸንኮራ አገዳ መትከያ ለስኳር ፋብሪካ ኢንቬስተሮች እየሸጠ ይገኛል።በርግጥ ልማት የሃገራችን ትልቅ እድገት ነው።የሚያሳዝነው ግን ኢትዮጵያ ብዙ ያልተነካ ብዙ የእርሻ መሬት አላት።ብዙ ለልማት የሚውል ቦታ ለማልማት ይቻላል።ይህ እየተደረገ ያለው ሆን ተብሎ ነው።ታሪክን ለማጥፋት ገዳማትና ሓይማኖት ለማጥፋት የታቀደ ድርጊት ነው።

ይህ ገዳም በኢትዮጵያ ከሚገኙት ገዳማት ትልቁና ብዙ መናኝ ያሉበት ነው።አሁን ደግሞ ከሰሞኑ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ላይ የጳጳሳትን ድርድር አከሸፎት ለራሱ በሚመቸው መንገድ የጳጳሳት ሹመት ሊያካሂድ ነው።ይባስ ብሎ በሶስት ወገን የተከፈሉት ጳጳሳት ሁሉም የየራሳቸውን አቋም ይዘዋል።አሁን የራሱን ካድሬ ጳጳሳት በመምረጥ በመሪነት አስቀምጧቸዋል።መንግስት የእምነትን ቦታ በአምባገነንነት በማንአለብኝነት እያሸከረከረው ይገኛል።ታዲያ ይህ በደል በሃገራችን ኢትዮጵያ እስከ መቼ ይቀጥላል?

# የኢትዮጵያውያን መከራ እንዴት ይቁም?

**Yonas Addisu/Coburg**

እኛ ኢትዮጵያውያን በህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት ላለፉት 22 ዓመታት ብዙ ችግሮችን አሳልፈናል።ብዙ ችግሮችን ለመጥቀስ እችላለሁ አሁን እየሆኑ ያሉትንና የተፈፀሙትን።ነገር ግን እኔ የማተኩርባቸው አሁን በግልፅ እየተፈጸሙ ያሉትንና ማንኛውም ሰው ሊያየቸው የሚችሉትን ብቻ ይሆናል።ተቃዋሚ ፓርቲዎች እነሱም በአገሪቷ ውስጥ ያሉት ምንም አይነት እንቅስቃሴ ማድረግ አይችሉም ።ስራቸውም በቢሮአቸው የተወሰነ እንዲሆን ተደርገዋል።በአገሪቷ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ማናቸውም ህዝባዊ ስብሰባዎችን ለማድረግ መብቶችን ተነፍገዋል።

ብዙ የታወቁና ልምድ ያላቸው የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾችና ነፃ ጋዜጠኞች በመንግስት ባለስልጣናት በወታደሮች በፖሊሶችና በደህንነት ሰዎች እየተዋከቡ ከአገር እንዲሰደዱ ተደርገዋል።ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት ጋዜጠኞች ህልውና አደገኛ አገር ሆናለች።

የመንግስት ባለስልጣናት በኢንቬስትመንት ስም ህዝቦችን ለዘመናት ከሚኖሩባትና ምርታማ ከሆነው መሬታቸው እንዲፈናቀሉ በማድረግ መሬቶችን እየሸጡ ይገኛሉ።በዚህም የተነሳ ህዝቦች ከለም መሬታቸው በግዳጅ ለም ወዳልሆነው መሬት እንዲወጡ በመደረጉ ወደጎረቤት አገሮችና ክልሎች እንዲሰደዱ ተደርገዋል።እነዚህና ሌሎች ችግሮች በኢትዮጵያውያን ላይ በአሁኑ ሰዓት እየተፈጠሩ ካሉት አንዳንዶቹ ቢሆኑም፣እነዚህን ለመቀየር ችግሩ የሚፈታው በኢትዮጵያው ን ትግል ብቻ መሆኑን አምናለሁ።

ስለሆነም በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ማንኛውንም ትግል መደገፍ ያለብን መሆኑንና በዚህም ትግል የአገሪቷና የህዝቦቿ ጠላት የሆነውን ይህንን መንግስት መጣል ይኖርብናል።ልዩ ልዩ መንገዶችና አካሄዶችን በመጠቀም ትግሉን ወደተፈለገው ዓላማ "ነፃነት ፍትህና ዴሞክራሲ" ማብቃት ይኖርብናል።

በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ቀድሞ ከሰሩት በተለየ መልኩ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

እባካችሁ ተቃዋሚዎች የኢትዮጵያውንን ትግል መርቶ የተሻለን ህይወት ለመፍጠር በጋራ መነጋገር ይጠበቅብናል።

አንድነት ይኸንን አስቸጋሪ የሆነውን የመንግስት እንቅስቃሴ ለመጣል ብቸኛ መንገድ ነውና አንድ እንሁን!እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።

# ወያኔ ጥፋት እንጂ ልማት አያውቅም !

**Selamawet Tamerat Amede/ Langenselbold**

ትላንት የተናገሩትን ዛሬ፤ ዛሬ የተናገሩትን ነገ የማይደግሙ ከሀዲ አንባገነን እና ዘረኛ ቡድኖች የስልጣን ኮርቻ በሀይል ከተፈናጠጡበት እለት ጀምሮ የተለያዩ የማወናበጃ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ የበርካታ ንጹሀን ዜጎችን ህይወት ቀጥፈዋል አስቀጥፈዋል፡፡እንኳን እንደጠላት የሚቆጥሩትንና በመርሃ ግብራቸው ነድፈው መጥፋት አለበት ብለው የፈረጁትን ህዝብ ቀርቶ አርነት እናወጣሀለን እያሉ ከእናንተ በመፈጠራችን ኮራንባችሁ የሚሏቸውን የትግራይን ንጹሀን ዜጎች ሳይቀር የራሳቸውን የስልጣን ዕድሜ ለማራዘም ውድ ህይወታቸውን እንዲገብሩ አድርገዋል፡፡ የሀውዜን ጭፍጨፋ አቀናብረዋል፣ በ1991ዓ.ም በኢትዮጵያና በኤርትራ መካከል በተደረገው ጦርነት ከ70ሺ በላይ የጦርነቱ ሰለባ ሆነዋል፡፡አልሻባብን ለመደምሰስ በሚል በሶማሊያ በረሃ የረገፉትን ወታደሮች ቤት ይቁጠራቸው፡፡

ስልጣን ለወያኔ ከምንም ነገር በላይ ነው፡፡ ስልጣን ከሉአላዊነት፣ከባህር በር ፣ከሀገርና ከህዝብ እንደሚበልጥባቸው ከመጀመሪያው ጀምሮ የወሰዷቸው እርምጃዎች ማሳያ ናቸው፡፡የገዛ ሀገሩን ቆርሶ ለሱዳን የሚሰጥ፣የባህር በር አያስፈልገኝም የአሰብን ወደብ ውሰዱት፣ኤርትራ እንድትገነጠል ፈቅጃለሁና እውቅና ስጡልኝ እባካችሁ እያለ የአለም መንግስታትን የተማጸነ፣የገዛ ዜጎቹን አፈናቅሎ ለውጭ ባለ ሀብቶች መሬታቸውን የሚሰጥ፤የሀገሪቱን ሀብት ለተደራጁ ወንበዴዎች የሚያስዘርፍና የሚዘርፍ፤ሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦችን አጥፍቼ ታላቋን ትግራይን እመሰርታለሁ ብሎ የሚንቀሳቀስ አንባገነን እንዴት ያለ ሀገራዊ ራዕይ ነው የሚኖረው?ስለዚህ አምባገነኑን ስርዓት ለማስወገድ ከአንድነት ሃይሎች ጋር እ ን ድ ን ሰ ለ ፍ ጥ ሪ ዬ ን አቀርባለሁ።

# ለጥሩ ውጤት ፍቱን ስርዓት

**Agegnehu Wubet/ Zeil**

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ኢትዮጵያ የትምህርት ፖሊሲ ስርዓትና የትውልዱ አቀራረፅ እንዲሁም የእውቀት ግንባታውን ስንመለከተው መላ ሊባል ያስፈልገዋል።

ምንም ቢባል የማያልቀው የወያኔ አምባገነን ስርዓት የዘረኝነት ብዤር የመሳሰሉ ነገሮችን በትምህርት ስርዓቱ ውስጥ በማስገባትና በመከፋፈል በፖሊሲው መሰረት መመራትና መራመድ ያለበትን ጥራት ሳይሆን ሽፋን የሚሉ ቃላቶችን በመጠቀም ዜጎች ተገቢውን እውቀትና ችሎታ ሳይዙ ራዕያቸው እየመከነ ይገኛል።

አጠቃላይ የመንግስት ስርዓቱ ፈራርሶ ግፍና ጭቆና በሁሉም ዘርፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል።በዚህም ምክንያት ሳይፈልጉ በግድ ለስደት የተጋለጡ በርካቶች ናቸው።በአገራቸው ሰርተው በመኖር የነገ ህይወታቸውን መለወጥ የሚፈልጉ ባለራዕይ ወጣቶች ተቃውሞ በማሰማታቸው ዛሬ ከጥያቄያቸው ጋር ምንም ግንኙነት በሌለው በአሸባሪነት ወንጀል ጭምር እየተከሰሱ መግቢያና መውጪያ አጥተዋል።

ታዲያ ይህን የወያኔ ተልዕኮ ለመከላከልና ጨርሶ ለማስወገድ ሃገርንና ወገንን ማዳን ይኖርብናል።ሰላምና ፍቱን ስርዓት ለኢትዮጵያችን!

# የዘር ማፅዳት ዘመቻ ዓለምአቀፍ ወንጀል ነው!

**Yohanes Samson/Bad Hersfeld**

የህወሓት/ኢህአዴግ መንግስት በኢንቬስትመንት በፖለቲካ እንዲሁም ከሰፈራ ጋር በተያያዘ እያደረገ ያለውን ሰፊ የህዝብ ማፈናቀል በጥብቅ እንቃወማለን።የኢህአዴግ የ21 ዓመታት ፖሊሲ ጎሳን ከጎሳ ሃይማኖትን ከሃይማኖት በማጋጨት በቢሊዮን የሚቆጠር ንብረት ውድመትና በሚሊዮን ለሚቆጠር ህዝብ መሰደድና በሃገር ውስጥ መፈናቀል ምክን ት መሆኑ ይታወቃል።በጋምቤላ አፋር ደቡብ ክልል ቦረና አርባጉጉ ኦጋዴን እንዲሁም በቅርቡ በቤንች ማጂ ጉራፈርዳ እና ቤኒሻንጉል በአማራ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ላለው የዘር ማፅዳት ዘመቻ የህወሓት ኢህአዴግ መንግስትና አጫፋሪዎች ተጠያቂ መሆናቸው ለማንም ግልጽ መሆን ይኖርበታል።

ይህን ዜጎችን የማፈናቀል እኩይ ስራ ደግሞ ከስልጣንና ከቂም በቀል የግል ጥላቻ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተባብረን ካላስቀረነው በስተቀር ዛሬ በአማራው ላይ የደረሰው ነገ በሌሎች ዜጎች ላይ እንደሚቀጥል ቀድመን ማወቅ ይገባናል።በተጨማሪም ከወንጀልነቱ ባሻገር ይህንን ሰው ሰራሽ የሆነውን የሰው ልጅ መከራና ስቃይ ለመቀነስ እኛ ኢትዮጵያውያን የተጫለንን ሁሉ ማድረግ ይገባናል።ይህንን አይነት አሰቃቂ ሁኔታ የወገኖቻችን የየት እንግባ የድረሱልን ጥሪን እየሰሙ እያዩ ዝም ማለት ከሞራልም ሆነ ከሰብዓዊነት አንፃር ትክክል አይሆንም።በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሄደ ያለው አስከፊ የሰብዓዊ መብት ረገጣ ይቆም ዘንድ እያንዳንዱ ዜጋ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት።



# የአቡኑ ውሸት

**Tedela Getenet Tafere/Germany**

ወያኔ መራሹ ዘረኛ መንግስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ለማጥፋት ኢላማውን ካነጣጠረ እነሆ 21 ዓመታትን አስቆጠረ።ወያኔ ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት በግልፅ የግድ ወታደር ማዝመት አይጠበቅበትም።ለምን ቢባል ገና በደደቢት እያለ ያሰለጠናቸውን ልዩ ሃይል መነኩሴ በማስመሰል አሰልጥኖ በመላክ ተልዕኮውን እያሳካ ይገኛል።

ታሪካዊውን የዋልድባን ገዳም በጅማ ያሉ አብያተ ክርስቲያናትን በስልጤ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን በአሸባሪዎች ሲቃጠሉ እንዲሁም በምዕራብ ጎጃም ጣና በለስ አካባቢ ያሉ 17 አብያተክርስቲያናት እንዲፈርሱ በወያኔ ሲወሰን አንድም የሃይማኖት አባት አለመቃወሙ ምንን ያሳያል?በቤተክህነቱ ያሉት ሁሉ የወያኔ ቅጥረኞች ናቸውና ይሁን ከማለት ውጭ ምንም አይሉም።ለመቃወም እንኳን ቢሞከር ጥቁር ቀለም በመቀባት ማሰቃየትን ያውቁበታል።

ካሁን ቀደም የነበሩት አቡነ ጳውሎስም ሆኑ አዲሱ 6ኛው አቡን ወያኔን በመደገፍ የሚታወቁ ናቸው።አሁንም ቤተክርስቲያናችን እውነተኛ አባት የላትም።ትክክለኛው አባት ያሉት በስደት ነው።

አሁን ማለት የፈለኩት አዲሱ ተሿሚ አቡን ከአሜሪካ ሬዲዮ ጋር ያደረጉት ቃለምልልስ ወሸት የበዛበት ነው።እኚህ አባት በመጀመሪያ ጨካኙን ደርግን በመደገፍና በማቀንቀን የሚታወቁ በመሆናቸው ወታደራዊው መንግስት የሚወስደውን እርምጃ ስለደገፉ ጳጳስ ሆኑ።ደርግ ቤተክርስቲያንን ለመዝጋት እቅድ ሲያወጣ ፓትሪያርኩ ሳያውቁት እንዲያውቁት የተደረገው አባ ማትያስ ናቸው።ታዲያ ይህ የሚያሳየው የደርግ አቀንቃኝ መሆናቸውን ነው።በቀጣይም ቅድስት ቤተክርስቲያን የጣለባቸውን አደራ በመዘንጋት ሃገር የካዱ የመጀመሪያው ናቸው።በዚህ ድርጊታቸውም የተወገዙና በምትካቸው ሌላ አባ ማትያስ ተሰየሙ። ደርግ ሲወድቅና የጥፋት መልዕክተኛው ወያኔ አገሪቱን ሲቆጣጠር የተወገዙት አቡን በማንአለብኝነት አገር ቤት ገቡ።መወገዜን አላውቅም አሉ ታዲያ እኒህ አባት አልዋሹም?እሳቸው የሚሉት አሁን በህወሓት የሌሉትን አባት በምስክርነት ይጠራሉ።ይህም የሚያሳየው አቡኑ የወያኔን የሃሰት ተሃድሶ የወሰዱ መሆናቸውን ነው።

በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ህዝብ መረጠኝ አሉ።ይህም ሃሰት ነው የመረጣቸው ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ካሉት አባቶች የተሻሉ ሆነው በወያኔ የታመነባቸው ስለሆኑ በጉልበት ተመደቡ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብ አልመረጣቸውም። ለማስመሰል ድምፅ እንዲሰጡ የተደረጉትም የወያኔ ካድሬዎች ናቸው። ታዲያ 6ኛው አቡን ገና አንድ ወር ሳይሞላቸው ይህን ያህል ከዋሹ ከቆዩማ አያድርስ ነው።እግዚአብሔር አምላክ ሆይ እነዚህን የሃሰትና የወያኔ ቅጥረኛን አስወግደህ ትክክለኛውን አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስን ወደ መንበረ ክብራቸው መልሰህ አሳየን አሜን!

# መተካካተ ወያኔ

**Kidane Gebregziabher/ Germany**

ነፍሳቸውን ይማርና ከሞቱ በሁዋላ የልማት አርበኛ መሃንዲስ......ወዘተ በመባል እየተነሱ ያሉት የአምስት ዓመቱ እቅድን ሲደሰኩሩልን እንተካካለን ብለው ነገሩን ለማስመሰል የተወሰኑ ሰዎችን እረፍት አስወጡ ወይም ተሃድሶ እዲወስዱ አደረጉ።ከዚያም ራሳቸው ሞቱ በወያኔያዊ መንገድ ሌላ ወያኔ ተተካ እሳቸው የሁሉም ነገር ፈጣሪ የሆኑት አንድም ሁለትም ሆነው ሲሰበሰቡ ስማቸው ይነሳል።ይወደሳሉ።ስለአገራቸው ከሳቸው ይልቅ ከፍተኛ ስራ የሰሩት እንኳን እንዲህ አልተነገረላቸውም።ግን ኢትዮጵያን ያለወደብ ያስቀሩትና የነገ አገር ተረካቢ የሆነውን ዜጋ ድብቅ በሆነ አሰራር የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኛ እንዲሆን በማድረግ የተጠመዱ ባለስልጣናት እንጂ ሃገርን በልማት የሚያሳድግ ንፀህ ዜጋ በማፍራት ላይ አይሰሩም።




ወያኔ የተጠመደው ዜጋን ከዜጋ የሚያጋጩ ጭንብል የለበሱ ካድሬዎችን መፈልፈል እንጂ ሃገር ተደፈረ የሚል አንድም ሰው እንዳይነሳ ትልቅ እንቅፋት መፍጠር ለምን የሚል እንኳን ቢኖር በሽብርተኛ ስም በመክሰስ ከመናሰቃየት በስተቀር ሌላ ስራ የላቸውም ኑሮ ተወደደ ለህዝባችን እንድረስለት የሚል መሪ የላትም ታዲያ ወያኔ መቼ ነው የሚተካካው?አሁን የሚደረገው ትልቁን ወያኔ በትንሹ ወያኔ መተካት ከሆነ የመተካካት ትርጉሙ ቃሉ ባይነገር ይሻላል ለምን ቢባል ለይስሙላ የተፈጠረ በመሆኑ ባይነሳ እመርጣለሁ።

አሁን በቅርቡ ወያኔ በባህርዳር ያደረገው ስብሰባ ቀልድ የልጆች ጨዋታ ስራ ነው።አቶ አዲሱ ከእረፍት ተመለሱ።አቶ ስዩምና አርከበ እንደ ጓደኞቸው ሃይል እንዲሰበስቡ በማድረግ ሲጠናቀቅ የአምስት ዓመቱ መርሃግብር አንዱን እያሳረፉ ሌላውን እንዲተካ ከማድረግ በስተቀር ምንም መፍጠር የማይችል መሆኑን አሳይተውናል።ይባስ ብለው የመለስ ቦታ ላይ ሰው እንዳይቀመጥበት ምስል/ጣኦት በማቆም አዲስ ስርዓት በማቆም አዲስ ስርዓት አሳይተውናል።መቼም ወያኔ አይናውጣነቱን አሳየን መለስ ምንም አይነት ጥሪት የለውም ይሉናል።ታዲያ እኛ እንድንተካላቸው ነው እንዲህ የሚሉት ትክክለኛውን መተካካት ካሰቡ ለህዝቡ ነፃነት ይሰጠውና ማንን እንደሚመርጥ ያኔ ይታያል።

መተካካት የሚባለው ተወዳድረው ሲያሸንፉ ለህዝቡ የተሻለ ነገርና አማራጭ ሲቀርብለት እንጂ ወያኔ አርፎ ወያኔ ቢተካ ያው ነው እንዲያውም የጠገበውን ወፍራም ወያኔ አሳርፎ አዲስ በላተኛ መተካት ነው እያየን ያለነው።ታዲያ ወያኔ በመተካካት ስም እየቀለደብን ስለሆነ ሁላችንም በጋራ ሆነን ወያኔን ከስሩ ነቅለን ለማጥፋት እንነሳ!

# ሳንከፋፈል አስከፊውን የወያኔ ሥርዓት በአንድነት እንታገለው

**Tokon, Paulos Tefera/Greding**

ሀገራችን ኢትዮጵያ ዛሬ የእድገትም ሆነ የታሪክ ጭራ ሆና በከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ የነበረው የሀገሪቱ ገጽታ በዚህ ትውልድ ጠፍቶ ዜጎቹ አሁን ባለው የፖለቲካ ረመጥ እየተጠበሱ ኢትዮጵያዊነታቸውን ቀምተዋቸው፣ ነፃ ፕሬስ ሕትመት ከልክለዋቸው፣ ጩኸት ሰሚ ርቋቸው፣ ሕግ ፍትሕ ሸሽተዋቸው፣ የሃይማኖት ነፃነት ነፍገዋቸው፣ ሕዝብ መሪ ሀገር መንግሥት ጠፍቷቸው ለይስሙላ በሚሠሩት ፍርድ ቤቶች እየቀረቡ ግማሾቹ የፍርድ ቤት ቁራኛ ሲሆኑ ከፊሎቹ እግሬ አውጭኝ ብለው ከሀገር ተሰደዋል። የቀረውም ከነገ ዛሬ ምን ይመጣ ይሆን ብሎ በፍርሃት ይጠብቃል ወይም ደግሞ የዘመኑ ባለሥልጣናት የሚናገሩትን ቃላት እንደገደል ማሚቱ እያስተጋቡ ለህሊና ሳይሆን ለሆድ አጎብድዶ እውነትን ክዶ ታሪክን ፍቆ እንደመንጋ እየተነዱ መኖር ብቻ ሆኗል። ምንም ይሁን ምን የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ገጽታ ቃላት ሊገልጹት በማይችሉ ውጥንቅጥ ችግሮች የተተበተበች ናት።

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚፈነጩት፣ የሚጠቀሙት የጎሳ ሹመኞች እንጂ ሌላው ሕዝብ ከወሬ በቀር ምንም ጠብ ያለለት ነገር የለም። ኢትዮጵያውያኖች በተወለዱበትና እትብታቸው በተቀበረበት ምድር ቤት ንብረት አፍርተው ልጅ ወልደውና አሳድገው ለአካለ መጠን እንዳይደርሱ በአዋጅ የተደነገገ ይመስል በደቡብ እና በምዕራብ ኢትዮጵያ በአማራ እና በኦሮሞ ተወላጆች ላይ የተፈጸመውን የተቀነባበረ ማፈናቀል እና ማዋከብ ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ጨለማን ተገን በማድረግ ቃጠሎ በማስነሳት የብዙ ዜጎች ሀብትና ንብረት የሚያወድመው የወያኔ አገዛዝ አንድ ሊባል ይገባዋል።

ይህ ሥርዓት የኢትዮጵያን ሕዝብ በቁም ቀብሮ ወያኔዎችን እንዲፍነሸነሹ ከማድረጉም በላይ በጋምቤላ ያደረሰውን የዘር ማጥፋት ወንጀል፤ አሁንም ንጹሐን ኢትዮጵያውያንን በጉልበታቸው በላባቸው ሞፈር ተሸክመው መሬት ምሰው ጥረው ግረው በሀገራቸው ምድር ላይ ያፈሩትን ቤት ንብረት እየወሰደ ከመኖሪያቸው የሚያፈናቅለውን ህሊና አለን፤ ሰብአዊነት ይሰማናል የምንል ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልናስቆመው ይገባል። እስከመቼ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደሚቀጥል ባይታወቅም በዓለም ዙሪያ የሚነፍሰው የለውጥ ነፋስ ለውጥን ከምንሻ ኢትዮጵያውያን ንቅናቄ ጋር ተጣምሮ ወደ ኢትዮጵያ ደርሶ በእስር እና በእንግልት ከሚማቅቁት እንደነ በቀለ ገርባ፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ፣ አንዱዓለም አራጌ እና ሌሎች በርካታ የፖለቲካ እና የህሊና እስረኞችን ከተከሰሱበት የተቀነባበረ የሀሰት የአሸባሪነት ክስ ነፃ እስከሚያደርግ፤ መላው የሀገሪቱንም ሕዝብ ከዚህ ጨቋኝ ሥርዓት እስኪታደገውና የወያኔ አገዛዝን ተጠያቂ እስከሚያደርገው ድረስ ሕይወት ናት እና ይህን አስከፊ ሥርዓት ሳንከፋፈል እኛ ኢትዮጵያውያን በያለንበት በአንድነት እንታገለው።

# የወያኔ ኣምባገነን ኣገዛዝ ይብቃ!


**Abraham Desta Gney/ Fulda**

የኢትዮጵያ ህዝብ ፈጣሪውን የሚፈራ፣ሀገሩን የሚወድ፣ተከባብሮና ተቻችሎ የሚኖር ኩሩና አስተዋይ ሕዝብ ነው። ይህ ኩሩና ጀግና ሕዝብ በየዘመኑ የገጠሙትን ፈተናዎች በረጋና በሰከነ መንፈስ ተወጥቷል። አሁንም ከፊቱ የተደነቀኑትን መሰናክሎች በብቃት፣ በአንድነትና በልብ ሙሉነት ይመክታል። የወያኔን ዘረኛና አምባገነናዊ አገዛዝም ከነሰንኮፉ ነቅሎ ለመጣል የሚያስችለው አቅም እንዳለው ቅንጣት አያጠራጥርም።

ሚያዚያ ሰባት ቀን 2005 ዓ.ም በተካሄደው የይስሙላ ምርጫ ለወያኔ አገዛዝና ለተቃዋሚዎች ግልጽ መልዕክቱን አስተላልፏል። ስለዚህ ይህን ዝግጁና ሀገር ወዳድ ህዝብ አስተባብሮ በመምራት የወያኔን ግብዓተ መሬት ማፋጠን የእያንዳችን ኃላፊነትና ግዴታ ነው። በተለይ በሰላማዊ ህዝባዊ እምቢተኝነት የምናም ሀይሎች በፌስ ቡክና በሌሎችም ማሕበራዊ ሚዲያዎች ላይ ተሰቅለን የምናወራበት ጊዜ ያበቃለት መሆኑን በመገንዘብ ወደ ለተግባር መነሳት ይኖርብናል ::



**የአማራ ብሔር ተወላጆች ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በቅርቡ ሲፈናቀሉ/Forced eviction of Amharas from Benishangul Gumuz region of Ethiopia/** በካርቱኒስት ብሩክ ገ/መስቀል



# አምባገነኖችን ለማጥፋት አንድ እንሁን!

**Mohammed Balcha Abdulha-kim/Frankfurt am Main**

በሃገራችን ኢትዮጵያ የዜጎች የመዘዋወር ንብረት የማፍራት የመኖር የመናገር የመምረጥና የመመረጥ መብቶች የሚወሰነው በጥቂት የህወሓትና ጀሌ ባለስልጣኖች መልካም ፈቃድ እንጂ በመሰረታዊ የሰው ልጆች መብት ድንጋጌ አይደለም።በሩዋንዳ የተፈፀመው የሰውን ልጅ ዘር የማጥፋት ድርጊት በአገራችንም ኢትዮጵያ በህወሓት ኢህአዴግ አማካኝነት እየታየ ነው።ዜጎች በማንነታቸው ከየት አካባቢ ብሔር ዘር ማንዘር ነው የመጣኸው/ሽው? እዚህ ለመኖር ለመስራት ንብረትን ለማፍራት ለመሳሰሉት የመኖሪያ ፈቃድ አለህ/ሽ ወይ? በሚል ብሄርን ከፋፍሎ መለያ በመስጠት ተከባብሮ የኖረውን ህዝብ በትውልድ አገሩ እርስ በራሱ ለማጋጨት እየተደረገ ያለው የዘገ የፖለቲካ ፖሊሲ የሃገራችንን ህልውና እየተፈታተነ ነው።

በብሄር ብሄረሰቦች ክፍፍል ላይ የተመሰረተ ዘርን በማጥፋት ፖለቲካ የተጠመዱት ወያኔዎች እንደ ሰደድ እሳት በአገራችን ዜጎች ላይ ያላቸውን ጥላቻ እያመላከቱን ይገኛሉ።በተለይም በቅርቡ በአማራው ላይ ተጠናክሮ የቀጠለው መፈናቀል በመባባስ ላይ ሲሆን፣ የጥፋት በትራቸው የገረፋቸው የአጋዬን የጋምቤላ የደቡብ ክልል የቤኒሻንጉል ጉሙዝ የዋልድባ የአባቶች የቅርብ ጊዜ በደሎች ሳይረሱ በበደል ላይ በደል በጨኸት ላይ ጨኸት እንዲበራከት ግድ ሆኗል።

ስለዚህ በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ያላችሁ ውድ ወገኖቻችን ይህንን አገዛዝ ለመጣል በአንድነት እንነሳ!

# ተስፋ በወጣቱ

**Rute Yohanes Tamire/Zeil**

ኢትዮጵያ የሚለው ስም ሲጠራ እና ድምፁም በጆሮዬ ሲገባ መላ ሰውነቴን የሚሰማኝ ስሜት አለ።ንዝረት የፍቅር ንዝረት ተስፋ የማጣት ንዝረት እንዲሁም በተስፋ የመሞላት ንዝረት ..... ብዙ ብዙ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል።ከእነዚህ ሁሉ ስሜቶች ተስፋ ትልቁን ቦታ ይይዛል።”ነገ ሌላ ቀን ነው”፤ይህ እውነታ ተስፋ ይሰጣል።ምክንያቱም ነገ ሌላ ሃገር ለማየት ያስችለናል።ይህም ተስፋ የተሻለች ያደገች ኢትዮጵያን ማየት ነው።

ታዲያ ይቺን የተሻለች ኢትዮጵያ እንዴት ማግኘት እንችላለን?ወጣትነት፡- የወጣትነት የእድሜ ክልል በአስተሳሰቡና በተግባሩ ሃገሩን ሊቀይር የሚያስችል ሃይል አዳዲስ ነገሮችን ከመፍጠር ችሎታ ጋር በሙላት የሚገኝበት በመሆኑ አንዲት ሃገር የተሻለ ነገን ማየት የምትችለው በወጣቱ ትውልድ አማካኝነት ነው።ይህን አባባል እውነት መሆኑን እናምናለን።

እስቲ ወደ እራሳችን ሃገር ዞር ብለን እንመልከት ....የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ የት ነው ያለው በምን አይነት ኑሮ ውስጥ ነው እያለፈ ያለው?የነገን የሃገሩን ሸክም ለመሸከም እንዴት ባለ ዘዴ እየተቀረፀ ነው? ይህ የለውጥ ትኩስ ሃይል ትውልድ በትምህርት በቤተሰባዊ ህይወት በሃይማኖታዊ ስነስርዓት በማህበራዊ የመተሳሰብ ህይወት የሚያስፈልገውን ክብካቤና ኩትኮታ እያገኘ ካላደገ ልፍስፍስና ለነገሮች ግድ የለሽ ይሆናል።በሃገሩ ላይ ብሎም በቤተሰቡ እና በራሱ ላይም የሚከሰቱትን ሁኔታዎች በደነዘዘ አዕምሮ ስለሚመለከት ትክክለኛ የማመዛዘን ችሎታውን አይጠቀምም።

በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን ስለ አየር ብክለት በተደጋጋሚ ሲነገር እሰማለሁ።በሃገራችን ጎልቶ የሚታየው ግን “የትውልድ ብክነት”ነው ብዬ ለመጥራት እዳዳለሁ።በወያኔ የ21 ዓመታት የግዛት ዘመን የትውልድ ብክለት ሊያስከትሉ የሚችሉ ጥፋቶች እየተሰሩ ነው።በትምህርት ብንመለከት ፖሊሲው አቅጣጫውን እንዲቀይር ተደርጓል።በባህል በማህበራዊ ኑሮ እና በብሄር አንዱ ሌላውን እንዲጠራጠር መተማመን እንዳይኖር የሚያደርጉ ሸኩቻዎች እንዲፈጠሩ ሆኗል።

የተሻለች ኢትዮጵያን ለማየት በእነዚህ ሁሉ ማደናበሪያዎች ሳንረበሽ ወጣቱን የመግራትና የማስተማር ግዴታችንን እየተወጣን አገራችንን አይዞሽ እንበላት እንተባበር እንንቃ አንድነት ይኑረን!

# ምንያህል መሸከም እንችላለን?

**Dejene Yirga Mulugeta/ München**

በሀገሪቱ ማዕዘናት ሁሉ መልካም ዜና አይሰማም። ከጋምቤላ እስከአፋር፣ ከቤንችማጂ እስከ አርሲ፣ ከአጋዴን እስከ ዋልድባ፣ ከቤኒሻንጉል እስከ ባድመ የግድያ፣ የዕገታ፣ የመፈናቀል እና የጦርነት ዜናዎች ዛሬም እየጐረፉ ነው።

የጐተራው ቀዳዳዎች እየበዙ ነው። መንግስት ደግሞ በግድ የለሽ አያያዝ ችግሮቹን ከቁጥጥር ውጪ እንዲወጡ እያደረገ ነው። በዚህ ሁሉ ላይ ደግሞ መምህራን እና አያሌ የመንግስት ሠራተኞች በተባባሰው የኑሮ ውድነት የተነሳ ከእጅ-ወደ -አፍ በሆነ ኑሮ በሞትና በሽረት መሃል በጣዕር ያዘግማሉ።

‹‹ደመወዙን የተቀበለ ሰው በቀዳዳ ከረጢት የያዘ እስኪመስል››ብዙዎቻችን በኑሯችን በረከትና መቅኖ አጥተናል።ልጆቻቸውን የሚያበሉት ያጡ ወላጆች ወደልመናና ደጅ-ጥናት እየተገፉ በሰው ፊት መለብለብ ግድ ሆኖባቸዋል።እናቶች የልጆቻቸው ከትምህርት የመምጫ ሰዓት ደረሰ ብለው እየተሳቀቁ ነው-የሚያቀርቡላቸው ቁራሽ እንጀራ በቤቱ ጠፍቷልና። ምግብ መመገብ ብርቅ የሆነበት ቤተሰብ ተቆጥሮ አይዘለቅም። ጐጆዎቻቸውን ዘግተው በረሃብ የሚረግፉ፣ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸው አቅመ-ደካሞች በየመንገዱ ዳር ከተገነቡት የሚያማምሩ ህንፃዎች ጀርባ ተከልለው ወደሞት እየተነዱ ነው። አረጋውያን በረሀብ ተሰቃይተው እየሞቱ ነው። በየመንገዱ ጥጋ-ጥግ በግራና በቀኝ የወዳደቁት አዛውንት እናቶች እና አባቶች ሰብሳቢ አጥተው ሲለምኑ ማየት መፈጠርን ያስጠላል። በየቤተክርስቲያኑ እና መስጂዱ ደጃፍ ኑሯቸውን የመሰረቱትም፤ የእኛን ምፅዋት በተስፋ እየተጠባበቁ እድሜያቸውን ይገፋሉ። ብዙዎች የሚላስ የሚቀመስ የላቸውም። በዋና ዋና አውራ-ጎዳናዎች አካፋይ ላይ እና በታወቁ አደባባዮች ዙሪያ በጠራራ ፀሐይ በደረታቸው ተዘርግተው የሚተኙ የጐዳና ተዳዳሪዎች መዲናችንን የረሃብ ቀጠና አስመስለዋታል።

በሽተኛ ወይም አረጋዊ ሳንሆን በየቤቱ ወጣት ገመምተኞች እጃቸውን አጣጥፈው ያለስራ ተቀምጠዋል። ልክ ህፃናት መዋያ እንደተበጀላቸው ሁሉ እኛም የአዋቂ-መዋያ ‘ተቀይሶልን’ በየጫት ቤቱ እንገኛለን። ግን ለምን?የኔሰው ገብሬ ለምን ለምን ሞተ? ለቀረነው የዚህ ዓይነት ‘ህይወት’ ለመተው ነው? ይሄስ ‘ህይወት’ለመባል የሚበቃ ነውን? መተንፈስና ቆሞ መሄድ ብቻ ‘ህይወት’ ሊባል ይችላል? ቀኑ ለአይን ያዝ ማድረግ ከመጀመሩ፡- በየተዘጉ ደጃፎች ፊት የሚኰለኰሉ ህፃናት ሴተኛ- አዳሪዎች ቁጥር በየለቱ እየጨመረ ነው።

ለአቅመ-ትዳር የደረሱ ሄዋኖችም ገላቸውን አራቁተው ለሽያጭ ቀርበዋል። የልጆቻችን እናቶች ሊሆኑ የሚገቡትን ቆነጃጅት በገንዘባችን ልንገዛቸው የምንችላቸው ሸቀጦች ሲሆኑ ማየት ምንኛ ያስቅቃል? በየአረብ አገራቱ ያሉ እህቶቻችን ስቃይም

እዚህ ካሉቱ ቢከፋ እንጂ አያንስም። በሊባኖስ የኢትዮጵያ ቆንስላ ፊት-ለፊት በአሰሪዋ እንደአስከሬን እየተጐተተች እና እየተደበደበች ያየናት ዓለም ደቻሳ፡- ኢትዮጵያዊነት በዓለም ህዝቦች ፊት የወደቀበትን እና የተዋረደበትን ደረጃ በግልፅ አሳይቶናል። ስለዚህ ይህንን አይነት ውርደት እስከመቼ ተሸክመን መኖር እንችላለን?

# ጠላትን ማወቅና ዕድሜውን ማሳጠር

**Abera Shiferaw/Germany**

ስለ ህወሓት ኢህአዴግ ላለፉት 40 ዓመታት ብዙ ተብሏል።በተለይም ላለፉት 22 ዓመታት የመንግስትን ስልጣን ከጨበጠ በሁዋላ ስለተፈፀሙት የሰብዓዊ መብት ረገጣ ጭቆና ዘረፋና ዘረኝነት ብዙ ተብሏል።ለሃያ ሁለት ዓመታት በወረቀትና በእስክሪብቶ እንዲሁም በተወሰኑ የሚዲያ ሽፋን የተደረገው ትግል የትም አላደረሰንም።በተወሰነም ደግሞ በጉሬላ ውጊያዎች የተደረጉት ትግሎች የጭቁኑን ታጋይ ህዝብ ደም ከማፍሰስ ውጭ የተገኘ ድል ብዙም አልታየም።ለትግሎቹ አለመሳካት ምክንያት ከነበሩት ውስጥ ደግሞ ትግሉ በተበታተነ መልኩ መደረጉ ዋነኛው እንደሆነ ይታመናል።አሁን ያለንበት ወቅት አንድ ነገር ይጠይቀናል።እሱም ትግሉን በአንድም በሌላ መንገድ እንዲሆን ማድረግ።

ህወሓት ኢህአዴግ የኢትዮጵያና የህዝቦቿ ጠላቶች መሆናቸውን ላለፉት ዓመታት በግልፅ አሳይተውናል።የኢትዮጵያ ህዝብም ከመቼውም ጊዜ በላይ ለድህነት ለስደት ለዘር ጥቃት ለእስር ለግርፋትና ለሞት ተዳርጓል።በተቃራኒው ጎራ ያሉ ተቃዋሚ የሆኑ ደግሞ ለግል ለቡድንና ለፓርቲያቸው ህልውና ሲሯሯጡ ሁሉም ትግል ውጤት አልባ ሆኖ ይገኛል።የህወሓት ኢህአዴግ ጭካኔ ግን እየበረታ በህዝቡ ላይ የከፋ የሰብዓዊ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ችግር እያስከተለ ይገኛል።ብዙዎቻችን ህወሓት ላቀረበልን የመከፋፈል ግብዣ ተገዢ ሆነን በዘርና በጎሳ ተከፋፍለን በየተራ ለሚደርስብን ጥቃት ተጋልጠን ኖረናል።

አብዛኞቻችን ዉጊያችን ከዋናው የጋራ ጠላታችን ከህወሓት ጋር ሳይሆን በሌላው ሰው ወይም ቡድን ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አስተሳሰብና ፕሮግራም ላይ ያነጣጠረ ነው።ስለሆነም ህወሓት ኢህአዴግ ላቀረበልንና ለዓመታት የሰጠንን የመከፋፈል የቤት ስራ እየሰራን እንገኛለን።

በተለይም ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ለመከፋፈል ችግር ተጋልጦ ቆይቷል።አሁን የሚሻለው ጠላትን ማወቅ ነው።የጋራ ጠላታችን ህወሓት ኢህአዴግ መሆኑ ይታመንበታል።ጠላትን ማወቅ ጠላትን ለማስወገድ የትግል ስልት መንደፍና ተግባራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ጊዜው የሚጠይቀው ጉዳይ ነው።ስለሆነም በውጭ የምንኖርም ሆንን በአገር ቤት ያለው ህዝብ አሁን ያለውን መከራ ለማስቆም የጋራ በሆነው ጠላት ላይ በተቀነባበረና በተጠና መልኩ በህብረት የትግል ስልትን በመንደፍና በመተግበር ትግላችንን ማፋጠን ይጠበቅብናል።ስለሆነም ግለሰቦች ቡድኖችና የፖለቲካ ፓርቲዎች በየትኛውም የትግል መንገድ ያሉ ሁሉ ልዩነቶችን በማጥበብ በመመካከርና ተግባራዊ ወደሚሆን የትግል እንቅስቃሴ ውስጥ በመግባት የህወሓት ኢህአዴግን ዕድሜ እንድናሳጥር እመክራለሁ።ውድቀት ለኢትዮጵያ ጠላቶች ይሁን!

# ይብቃን የወያኔ በደል

**Meron Berhane/Zeil**

የኢትዮጵያ ህዝብ ከአምባገነኖችና ከአረመኔዎች መቼ ነው ነፃ የምንወጣው? በጣም የሚገርም ነው።ሰው እንዴት በአገሩ ህዝብ በወገኑ ላይ እንዴት ይጨክናል? መሪዎች ለህዝባቸው መልካም ነገር ቢሰሩ በህዝባቸው ይወደዳሉ።በሰላም በጤና ይኖራሉ ክብርም ይኖራቸው ይሆናል።አሁን በኢትዮጵያ እየተሰራ ያለው ሰዎች በፖለቲካ አመለካከታቸው ይታሰራሉ ከስራ ይባረራሉ ይገደላሉ ከአካባቢያቸው ይፈናቀላሉ ይሰደዳሉ።የትምህርት እድል አይሰጣቸውም ይሄ ሁሉ በዛች አገር ላይ እየተፈፀመ ያለ ድርጊት ነው።ወያኔ 22 ዓመታት ሙሉ ግፍ በመፈፀም ላይ ይገኛል።

ስለዚህ ኢህአዴግ ሰራሽ ችግር ለማስወገድ አገሬ ናት የምንል ዜጎች ሁሉ በአገር ማዳን ትግሉ ውስጥ እንድንሳተፍ ታሪካዊ የትውልድ ሃላፊነት እንዳለብን አውቀን የበኩላችንን እንድንወጣ አደራ እላለሁ።

# አዲሱ ትውልድ እውነት ሳያይ እውነት ሳይሰማ ሞተ!

**Ibrahim Jusuf Suleyman/Alsfeld**

አምባገነኑ አገረ ገዥ የኢትዮጵያው አሻንጉሊት መንግስት ህዝቡን ለመከራ ለሰቆቃ ለችግርና ለፍዳ እያጋለጠው እንዲሁም አገሪቱን ለችግርና ለሰቆቃ እየዳረጋት ይገኛል።ይህ ችግር ፈጣሪ አምባገነን መንግስት አገር የማስተዳደርም ብቃት የለውም።ይህ አምባገነን መንግስት አገሪቱን እጅ ተወርች አስሮ እንዳታንሰራራ እያደረጋት ይገኛል።የአገሪቱን የትምህርት ፖሊሲ ብናይ ትውልድ ገዳይ መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። ተቃውሞውን ለማስማት የተንቀሳቀሰውንም የተማሪ ሃይል በአስለቃሽ ጋዝ በመበተን የአካልና የህይወት መስዋዕትነት እንዲከፍል አስገድዶታል።

አምባገነኑ ስርዓት ታሪካዊ የሆነውን አንድ ህዝብ በማሸበር ሃገርን ማፈራረስ የዘወትር ተግባሩ አድርጎታል።የወያኔ መንግስት በባህል በታሪክ በቋንቋና በደም የተሳሰረውን ህዝብ በጎሳ በሃይማኖትና በዘር እየከፋፈለ እኛ ኢትዮጵያውያን ለሰላም ለፍቅርና ለአንድነት ያለንን ቃል ኪዳን ለማፍረስ ሌት ተቀን እየማሰነ ነው።በዚህም ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ህዝቦች ተከባብረውና ተሳስበው ድንበራቸውን በማፍረስ ጭምር በጋራ እየኖሩ ባለበት ዓለም፤ዓለማችን ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠችበት ባለበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ግን የእውነት አገራዊ ስሜት ያለው መንግስት አጥታ ህዝቦቿ ለችግር ተዳርገው አሳረ መከራቸውን እያዩ ነው።መቼ ይሆን በኢትዮጵያችን ዴሞክራሲ ሰፍኖ ፖለቲከኞችም ከስደት ተላቀንና በአገራችን ሆነን አዲሱ ትውልድ እውነት አይቶ እውነት ሰምቶ ይህችን ዓለም የሚሰናበትባት?መች ይሆን?

# ፀረ-ሃይማኖቱ የወያኔ መንግስት

**Priest Gebremariam Mulualem/ Germany**

ወያኔ በደደቢት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከፍተኛ የጥፋት ተልዕኮዎችን አንግቦ የተመሰረተና በዚህ ሰይጣናዊ ተልዕኮው በመሰማራት ትውልድ ይቅር የማይለው ጥፋት እያደረሰ ይገኛል።ወያኔ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ያደረሰውን ጥፋት እያንዳንዱን ለመፃፍ አይቻልም።ከምስረታው ጀምሮ ለጥፋት የተቋቋመ የይሁዳ ደቀመዛሙርት ናቸው ማለት ይቀላል።እንዲያው የረጅሙን የውድመት ዘመን ትተን አሁን በቅርቡ እያደረሰ ያለውን በአጭሩ እንጥቀስ።



በኢትዮጵያ ውስጥ አረመኔ በመባል የሚታወቀው ደርግ ነው።ነገር ግን ደርግ አጥፊ ቢሆንም የኢትዮጵያን ውድ ቅርሶች ያስጠበቀ ያልዘረፈ የተከበሩ ቦታዎችን እንኳን አክብሮ የያዘና የጠበቀ ነው።ወያኔ ግን በማንም ዘመነ መንግስት ያልተነኩና ተከብረው የኖሩትን ታላላቅ ቦታዎችን ታሪካቸውን ያጠፉ አጥፊ ነው።ደብረ ዳሞ የአሰቦት ገዳም የእቋላ ገዳምን እንዲቃጠሉ ያደረገ በሁዋላም ታላቁን የዋልድባ ገዳምን ቦታ ለስኳር ልማት መዋል አለበት በማለት አጽመ ቅዱሳንን የደፈረ በአካባቢው የነበሩትን አብያተክርስቲያናት እንዲፈርሱ ያደረገ ካመት እስከ ዓመት ለሃገር ለወገን የሚፀልዩ አባቶችን ከገዳም ያስወጣ ያሰረ ያንገላታ እናንተ አማሮች ናችሁ ብሎ ያስወጣ የዳቢሎስ የበኩር ልጅ ወያኔ ነው አሁንም በቤተክርስቲያናችን ላይ እያደረሰ ባለው ዘመቻ ያልረካ የጥፋት ዘመቻ ተጀመረ እንጂ ገና አልተጠናቀቀም።

ስለዚህም ወገኔ የኢትዮጵያ ህዝብ ወይ ንቃ ወያኔ የጥፋት መልዕክተኛ መሆኑን እንወቅ።የቤተክርስቲያናችን አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስን ከመንበራቸው በማንሳቱ ስለገዳማቱ ጥያቄ የሚያቀርብ አባት አጣን የሚመደቡትም የወያኔ ቅጥረኛ ስለሆኑ ለገዳማቱ የሚያዝን የሚጠይቅ አባት የለንም። ታዲያ ይህንን ድርጊት በዝምታ ማለፉ ትዝብትን ያስከትላል።ዛሬ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ላይ የጥፋት ድግስ ተደግሷል ነገ ዕጣው የማን እንደሆነ ስለማይታወቅ ከደንቃራው ችግር ተምረን በአንድነት እንነሳ እላለሁ። እግዚያብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።አሜን!

# ድምፃችን ይሰማ!

**Hiwot Tilahun/Zeil**

በአሁኑ ጊዜ የትኛው የኢትዮጵያ ዜጋ ነው ያልተገደለ ያልተዋረደ ያልታሰረ ያልተጋዘ የትኛው የኢትዮጵያ መሬትስ ነው ያልተመዘበረ ?ያልተበረበረ ማነው? በኢትዮጵያዊነቱ ያለፍርሃት ያለመሸማቀቅ በዜግነቱ ተከብሮ መኖር የሚችለው ከአምባገነን አሽከሮችና አባላት በስተቀር ማነው በእውቀቱና በችሎታው ተወዳድሮ ሰርቶ ለመኖር የሚችለው ?ማንም አይኖርም በግምት አይደለም ሃቁ ማንም የለም እንደ ውቂያኖስ ከላይ ሲታይ ፀጥ ብሎ የሚታይ በውስጧ ግን የኢትዮጵያ ህዝቦች በስቃይና በመከራ እየተቆሉ የሚገደሉባት የራሷ ዜጎች እንደ ስጋ ትል በሚርመሰመሱ ዘረኛ ቡድኖች አባላት የሚበሉባት የገሃነብ ገንዳ ሆና ሳለ እንዴት አይናችንን ጨፍነን ጆሮአችንን ደፍነን ህሊናችንን ከደን እንዴት በዝምታ እሺ ብለን በሰላም ስም ግፍ እየተፈጠረብን እንዴት እንኖራለን?

በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በአማራ ላይ የሚደርሰው ግፍና በደል ከመቼውም ጊዜ በላይ እየባሰ መጥቷል።እንዴት የአንድ አገር መሪ በሚመራው ህዝብ ላይ እንዴት የአንድን ዘር በተናጠል የማጥፋት ዘመቻ ለማካሄድ ምን ታስቦ ነው?በተለይ የአማራውን ብሄር በተናጠል የማጥፋት ዘመቻ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ጋር መኖር በመቻሉ ወደፊት በስልጣኔ ላይ ከፍተኛ ችግር ነው ብሎ በማሰብ በዚያ ምክንያት የአማራ ህዝብ ከኖረበት ሃብት ካፈራበት ቦታ ላይ እያባረረው ይገኛል።በተለይ ከዚህ በፊት በበደኖ በአረካ በጅማ በወሮጉቱና በሌሎች አካባቢዎች በተለያየ ጊዜ በአማራው ብሄር ላይ የማፈናቀል ዘመቻ ዘረኛው አምባገነን መንግስት አድርጓል።

አሁንም በአማራው ላይ የደረሰው ግፍ የሰማነው ተቃውሞ አሁንም በቡራፈርዳ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልና በሌሎች ክልሎች በዘረኛው የወያኔ ቡድን የሚካሄደውን የአማራ ዘር ለይቶ የማጥፋት ፋሺስታዊ ዘመቻ በመቃወም ድምፃችንን ማሰማት አለብን።ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

# ከእሾህ የተጠጋ ቁልቋል ሲያለቅስ ይኖራል!

**Ethiopia Lemma/Dreieich**

ተከላካይ ቅርንጫፍ ወይም ፍፁም የቅጠል ዘር የሌለው ይህ ቁልቋል አበቃቀሉ በበረሃ አካባቢ ነው።እንደ ጎረቤቱ እሾህ ሃይለኛ ያልሆነ እሾህም አለው የአህያ ባል ከጅብ ኢያስጥል አይነት ክፉ ጎረቤት እቃ ያስገዛል አይነትም አይደለም። የዛሬዎቹ ገዢዎቻችን ግን በትግሉ ጊዜ ለምግብነት ተጠቅመውበታል።ታዲያ ነፋስ ባወዛወዘው ቁጥር ከእሾህ ጋር ሲላተም ሆድ እንደባሰው ልጅ እንባውን ያጎርፋል።አማራውን ከጋምቤላው ሶማሌውን ካፋሩ እስላሙን ከክርስቲያኑ እያላተሙ እንባችንን የቁልቋል እንባ አድርገውታል።እነሱስ ያግበሰበሱት አልበቃ ብሏቸው ይሆናል ከቶ እኛ በውጭ የምንኖረው ምን አዚም ነክቶን ነው 22 ዓመት ሙሉ እጅ መስጠታችን? እኛ በውጭ ያለነው በቂ መረጃ እያለን በአገራችን የሚፈፀመውን ግፍ እየሰማን የስንቱ ወገኖቻችን ቤት በላያቸው ላይ ፈረሰ?ስንቶች ከተወለዱበት ቀዬ ለቀው ተሰደዱ ስንቶች ወነድም እህቶቻችን በዚህ ዘረኛ አገዛዝ ተማረው የሲና በረሃ በላቸው? ታዲያ ይህ ግፍ ያልተሰማን መቼ ሊሰማን ነው?ወይስ በእያንዳንዳችን ቤት እስከሚንኳኳ ድረስ መጠበቅ አለብን_አሁን ለእኔ እንደሚሰማኝ ተው የኔን እግር ነው የሚቆረጥም ዝም ብለህ ተኛ እንዳለው ሞኙ ሰው የሆነ ይመስለኛል።ከእነዚህ አምባገነኖች የምንላቀቀው በዚህ አይነት የትግል ስልት ከሆነ ገና ሌላ 22 ዓመታት ይገዙናል።መችም መች ተጀመረና ከተኩላ ዝምድና ነውና ይህ ግፍ እዚህ ላይ ይቁም።ለልጆቻችን አናውርስ በቃ እንበለው!እንደ ቁልቋል ስናለቅስ አንኑር ።አዲስ ዘመን አዲስ ቀን አዲስ ተስፋ አዲስ ራዕይ ለተጎሳቆለው ወገኔ ይሁን ኢትዮጵያዬ አንድነቷ ይኑርልኝ።

# ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም!

**Hanna Abebe/Germany**

የአቶ መለስ ዜናዊ ሞት በኢትዮጵያ ላይ ወይም በፖለቲካው ላይ የተወሰነ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣል ተብሎ ቢጠበቅም በተግባር እየታየ ያለው ግን የስልጣን ሽግሽግ ነው።

ነገር ግን በዜጎች ላይ በተለይ በአማራው ብሄር ላይ ግፉ በደሉ እስሩና ግድያው ተጠናክሮ በመቀጠሉ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ነው።ሆኖም ለአገሪቷም ሆነ ለህዝቧ ምንም አይነት እፎይታ የሰጠ አይመስለኝም።እነዚህን ጉዳዮች በተለይ በአማራው ህዝብ ላይ በሚደረግበት የማጥፋት ዘመቻ ያልተነካ ኢትዮጵያዊ የለም።መሪዎቻችን አማራው የራሳቸው ወገን እንዳልሆነ ነጥለው ማጥቃታቸው ምን እንደሚያመለክት ለሁሉም ግልፅ ነው። **ታዲያ እስከመቼ?**

እነዚህ አሳዛኝና አሳሳቢ ጉዳዮች በአገራችን ዜጎች ላይ ተጠናክሮ የቀጠለውን ግፍና በደል ለማስቆም አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በጋራ ሆነን ጩኸታችንን ማሰማት አለብን እላለሁ።ሰላም ለአንዲቷ ኢትዮጵያችን!

**We are the voice of the voiceless ! RESPECT Press Freedom in Ethiopia!!!**

PO **የግጥም ቋት** EMS

# አመፁ ይቀጥላል!

**Nebyu Tefery-Mekonen/ Flörsheim**

አመፁ ይጧጧፍ በተገኘው መንገድ
መዘናጋት ያብቃ ወያኔ ይወገድ።
ከወያኔ ከማለም ዴሞክራሲና መብት
ይቀላል መሞከር ከድንጋይ ላይ ወተት።
በሕወሓት መሰንጠቅ ሰላም የሚመኝ
ሰው
ከእባብ እንቁላል እርግብ መጠበቅ ነው።
መለስን ሲያነሳው አምላክ በቃህ ብሎ
ሌጋሲ አራማጁ ወጣ ተኮልኩሎ።
መላ አገሪቷን በዘር ቅርጫ አድርገው
የውስጥ ወራሪዎች በውጭ ተረድተው
ዜጋውን ባገሩ በባርነት ረግጠው
እየጨፈጨፉ ዘር ማጥፋት ላይ ናቸው።
ሞት እንደሆን አይቀር ምንድነው ፍርሃቱ
ወያኔ ይደምሰስ ከስር መሰረቱ
በትግራይ አይነግድ ይወገድ ስርዓቱ
ዘረኞች ያላዝኑ ደረት እየመቱ
ኢትዮጵያ አንድ ናት ነገም እንደ ጥንቱ።

# የትግሉ ነው ሕይወቴ

**Asefa Mengistu/ Vlotho**

ለዘመናት በጭቆና ማጥ
በግፍ ሰንሰለት ታስሬ
መብቴን ላስከብር ጨቋኙን ልሽር
ተነስቻለሁ ዛሬ
ይኸው ታጥቄአለሁ ዛሬ
ባንድ እንደሚነሳ ተበዝባዡ ሁሉ
ለማያጠራጥር ድሉ
ፍፁም ነው እምነቴ
የትግሉ ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና
በተሰውት ጓዶች ፋና
የመደብ የብሔር ጭቆናን
እስከማጠፋ ትግሌን ልቀጥል
ርሃብ አይገታኝም ችግር አይፈታኝም
ከግቤም አያግደኝም
ፍፁም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰውት ጓዶች ፋና
የህዝቡ ታማኝ አገልጋይ ነኝ
የህዝቡ ወታደር
ጠላት ይፈር ይሸበር
ያድርባይ ቅስሙ ይሰበር
ቢወቀጥ አጥንቴ ቢንቆረቆር ደሜ
ለአዲስ ስርዓት ልምላሜ
ፍፁም ነው እምነቴ የትግሉ ነው ሕይወቴ
ልጓዝ በድል ጎዳና በተሰውት ጓዶች ፋና (2)

# ለማን አቤት እንበል?

**Genet Zewdie Wondmu/ Duisburg**

ለማን አቤት እንበል ወደማን እንጩህ
ሓገር ስትጠፋ ምድር ስትራቆት
እየተቆረጠች ለባዕድ ስትሸጥ
ሰው ከኖረበት ሲባረር ሲሰደድ
ለማን አቤት እንበል ወደማን እንጩህ
ምርቱ ተለቃቅሞ ከሃገር ሲወጣ
ሃገር ውስጥ ያለው የሚበላው ሲያጣ
ችግር አቆራምዶት ልመና ሲወጣ
ለማን አቤት እንበል ወደማን እንጩህ
ምረጡኝ እያለ ህዝቡን ሲያስጨንቅ
አልመርጥም ያለውን ከስራ ሲያስለቅቅ
ተማሪውን ደግሞ በዱላ ሲያደቅ
ለማን አቤት እንበል ወደማን እንጩህ
ሽማግሌዎች በሃገር ውስጥ መኖር አቅቷቸው
ወጣቶች በአገር ውስጥ መማር አቅቷቸው
ስደትን መረጡ ወጡ ከአገራቸው
በየበረሃው ላይ ወደቀ ሬሳቸው
ሽፍቶች ኩላሊታቸውን አርደው ሲቀሟቸው
ለማን አቤት እንበል ወደማን እንጩህ
ስለዚህ ወገኔ ማንም አያድነን እንወቅ ቁርጡን
ይልቅ እንነሳ በአንድነት እንሁን!
አማራ ኦሮሞ ትግራይ ማለቱን ትተን
ጥንት አባቶቻችን እንዳቆዩልን
አገራችንን እንጠብቅ በአንድ ላይ ሆነን!

# ዛሬም ያልደረቀው የአማራ ህዝብ እንባ!

**Yared Tadese Abraham/Hof**

እንደሚታወቀው የወያኔ ዘረኛ ቡድን ከጫካ ጀምሮ የአማራን ህዝብ በጨቋኝነት በመፈረጅ የማጥላላት ዘመቻ ሲያደርግ ቢቆይም እንደመንግስት ሥልጣን ሲይዝ በአማራ ህዝብ ላይ የሚያደርገውን የጥቃት መጠን ይበልጥ በማስፋት በግልፅ እና በህቡዕ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተፈፀመ ያለው የዘር ማጥራት ዘመቻ የአማራ ብሔር ተወላጆችን ብቻ በተለየ ሁኔታ የጥቃቱ ኢላማ ያደረገ ሲሆን በዚህም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ አማራዎች ቤት ንብረታቸው እየተዘረፈ በግፍ እንዲፈናቀሉ በዚህም ምክንያት ለበርካታ ስቃይ እና እንግልት እንዲጋለጡ የተደረገ ሲሆን ከፊሎቹ ዛሬም ድረስ ወዴት እንደደረሱ ሊታወቅ አልቻለም።
ይህ የወያኔ ዘረኛ ቡድን በአማራ ህዝብ ላይ እየተፈፀመ የሚገኘው የዘር ማጥራት ወንጀል ሀገራችን ኢትዮጵያን በዘር በሚነሣ ግጭት እንድትታመስ ከማድረጉም ባሻገር ደም አፋሳሽ ወደ ሆነ አጠቃላይ ግጭት ሊያመራ የሚችልበት ዕድል እየሰፋ መጥቷል።

በመሆኑም የሀገራችን ህዝቦች በዜግነታቸው እና ሰው በመሆናቸው ብቻ እንጂ በብሔር ማንነታቸው የማይመዘኑበት ፍትሀዊ የዴሞክራሲ አስተዳደር ለመገንባት እንዲሁም ሀገራችን ላይ እያንዣበበ ካለው ደም አፋሳሽ የዘር እልቂት ለመታደግ ዘረኛውን የወያኔ መንግስት በተባበረ ክንዳችን ልናስወግደው ይገባል።

# አሁንም አልተሳካም!

**Gizachew Dametew Fikre/HOF**

ወያኔ ወደ ሥልጣን የመጣውም ሆነ በሥልጣን የቆየው በህዝብ ምርጫና ፍላጎት ሳይሆን በጠመንጃ አፈሙዝ በታገዘ አፈና እንደሆነ የታወቀ ነው።ይሁን እንጂ ወያኔ ለይምሰልም ቢሆን በሚያዘጋጃቸው ምርጫዎች አንድም ጊዜ ቢሆን የህዝብን ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም።ለምሳሌ በዚህ አመት ሚያዝያ ወር በተደረገው የአካባቢ ምርጫ ላይ ምንም እንኳን ቁጥራቸው ሰላሳ ሶስት /33/ የሚደርስ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አስቀድመው ራሳቸውን ከምርጫው ያገለሉ ቢሆንም ወያኔ ምርጫው በተካሄደበት ዕለት ከህዝቡ ያገኘው ምላሽ ክፉኛ አስደንግጦት አባላቱንና ካድሬዎቹን ለግምገማ እንዲጠራ አድርጎታል።በዕለቱ ተከስተው ከነበሩበት ተግባራት መካከል የምርጫ ካርድ ከወሰዱት መካከል ገሚሱ ያልተገኘ ሲሆን በሥፍራው ከተገኙት መካከል አብዛኞቹ በምርጫ ካርዱ ላይ ወያኔን የሚቃወሙ ፅሑፎችን በመፃፍ ለአገዛዙ ያላቸውን ጥላቻ ገልፀውበታል።

በእርግጥ አስተዳድረዋለሁ በሚለው ህዝብ ክፉኛ የተጠላው የወያኔ አስተዳደር እስከመቼ በኃይልና በአፈሙዝ በታገዘ አፈና ህዝባችንን ይገዛል?መፍትሔው አንድ ብቻ ነው።ይኸውም በተቀናጀና በተደራጀ ሁኔታ የፖለቲካ ፕሮግራም ልዩነታችንን ለጊዜውም ቢሆን ወደ ጎን በማድረግ የጋራ ጠላታችን የሆነውን የወያኔ ቡድን ማስወገድ እና በቦታውም ሁሉን አቀፍ የሆነ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም ማድረግ ሲሆን ለዚህም የሁላችንን የጋራ ጥረት ለሚጠይቅ ትግል በህብረት እንነሣ!!!ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# "ጠብ ሲል....ስደፍን"

**Yohannes Selamu Benti/Hof**

በኢትዮጵያ ከተሰሩ የንግድ ማስታወቂያዎች መካከል በአይረሴነታቸው ዛሬም ድረስ በብዙዎች ህሊና ተቀርፀው ከሚገኙት መካከል ስለቤት ጣራ ክዳን ቆርቆሮ የተሰራው "ጠብ ሲል .... ስደፍን" የሚለው አንዱ ነው።ቆርቆሮው ከመቀደድ አልቦዘነም፥የቤቱ ባለቤትም ቀዳዳውን ከመድፈን እንዲሁ።ከዚሁ ታሪክ ጋር በይዘት የሚመሳሰል ተግባር በአለማቀፉ ማህበረሰብና በወያኔ መካከል እየተፈፀመ እነሆ ዛሬ ላይ ደርሰናል።

የወያኔ መንግስት ከጦር መሳሪያና ከታጠቀ ኃይል ባልተናነሰ ብዕርንና የሚፅፉ እጆችን እጅግ አጥብቆ ይፈራል።በመሆኑም በሰበብ አስባቡ በአካል ኢትዮጵያ ውስጥ ኖሩም አልኖሩ ክስ ይመሰርትባቸዋል፣በአሻንጉሊት ዳኞቹ አማካኝነት በራሱ የካንጋሮ ፍርድ ቤት ከሶስት ዓመት እስር ጀምሮ እስከ ሞት ይፈርድባቸዋል።በተለይ በሀገር ቤት የሚገኙ ከሆኑ በነዛ አስከፊ የወያኔ እስር ቤቶች እንዲማቅቁ ያደርጋል።

በተቃራኒው ወያኔ "አሸባሪ"፣"መንግስትንና ህገ-መንግስታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ ያሴሩ"፣"በዘር ማጥፋት ወንጀል ሙከራ ተባባሪ የሆኑ"..... እያለ የፈረጃቸውንና ያሰራቸውን ጋዜጠኞች ቀሪው የአለማቀፍ ማህበረሰብ ሃሳብን በነፃነት ለመግለጽ የሚዋደቁ ጀግኖች እያለ በክብር ላይ ክብርን እንዲያገኙ ከማድረጉም በላይ ብዙዎች ተመኝተው ያላገኙትን አለማቀፍ ውድ ሽልማቶችን ሲሸለሙ ታዝበናል።ወያኔ "አሸባሪ" እያለ ያስራል፤ዓለም ግን የነፃነት ታጋዮች እያለ ይሸልማቸዋል!

ለምሳሌ ያህል ለመጥቀስ፦ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ *(በወያኔ 3 ዓመት ታስሮ የተፈታ ነገር ግን በአለማቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተሟጋች ድርጅት ሲ.ፒ.ጄ. የተሸለመ)*፣ጋዜጠኛ ኤልያስ ክፍሌ *(በሌለበት ሁለት ጊዜ በወያኔ ተከሶ የዕድሜ ልክና የሞት ፍርድ የተፈረደበት ነገር ግን ለፕሬስ ነፃነት እያደረገ ባለው አስተዋፆ የተለያዩ ሽልማቶችን ሲ.ፒ.ጄን ጨምሮ ከተለያዩ አለማቀፍ ድርጅቶች የተቀበለ)*፣ጋዜጠኛ አበበ ገላው *(በሌለበት በወያኔ የካንጋሮ ፍርድ ቤቶች የ18 ዓመት እስራት የተፈረደበት ነገር ግን ለፕሬስ ነፃነት ባደረገው አስተዋፆ ከተለያዩ አለማቀፍ ድርጅቶች የተሸለመ)*፣ጋዜጠኛ ሠርካለም ፋሲል *(በግፍ ታስራና ሰብዓዊ መብቷ ተገፎ በወህኒ እንድትወልድ የተገደደች ነገር ግን ለፕሬስ ነፃነት መከበር ላደረገችው ብርቱ ተጋድሎ ከሲ.ፒ.ጄ. እና ሌሎች አለማቀፍ ተቋማት የተሸለመች)*፣ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ *(ዛሬም ድረስ በግፍ በወያኔ እስር ቤት የሚማቅቅ ነገር ግን 'ፔን አሜሪካ' የሚባለው ድርጅት በ2012 ዓ.ም. ምርጥ ጋዜጠኛ ብሎ በሌለበት የሸለመው እንዲሁም ከዚያ በፊት ለፕሬስ ነፃነት ላደረገው አስተዋፆ አለማቀፍ ሽልማቶችን የተቀበለ)*፣ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ *(በወያኔ እስር ቤት ህክምና ሁሉ ተነፍጓት በግፍ እየተሰቃየች ያለች ነገር ግን በዚህ አመት ብቻ ዩኔስኮ ምርጥ ጋዜጠኛ ብሎ በሌለችበት ሲሸልማት ሲ.ፒ.ጄም እንዲሁ የአመቱ ምርጥ ጋዜጠኛና ለፕሬስ ነፃነት ዋጋ የከፈለች ሲል ሸልሟታል)* ፣............እንግዲህ ስለ ጋዜጠኛ መስፍን ነጋሽና ውብሸት ታዬ እንዲሁም ስለሌሎች እንዳልተርክ ጊዜ ያጥረኛል።ነገር ግን እነዚህ ሁሉ ስለፕሬስ ነፃነትና ሃሳብን በነፃነት ስለመግለፅ ሲሉ ዋጋ የከፈሉ ብሔራዊ ጀግኖቻችን ናቸው።

ዛሬም አፈናው እንደቀጠለ ነው።ዜጎች በፍርሃት ተሸማቀው የሚኖሩባት ሀገር፣ጥቂት የወያኔ ካድሬዎችና ጀሌዎቻቸው የሀገሪቷን ሀብትና ንብረት በመዝረፍ የሚፈነጩባት ሀገር፣አብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል ከድህነት ወለል በታች የሚኖርባት ሀገር.........

እናም ዛሬ ለሀገራችንና ለህዝባችን ነፃነት ለመዋደቅ በጋራ የምንነሳበት ወቅት ላይ እንገኛለን።በህብረት እንነሣ፥በጋራ እንታገል።ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

# ያልታበሰው የሉሲ እምባ

**Atnaseiy Tesfaye Wegayehu/ Nürnberg**

**"የመከራሽ ትብታብ ቋጠሮም ለቀቀ፣**
**የገላሽ ኪንታሮት ቡግንጁ ወደቀ፣**
**ብዬ ስመኝልሽ ፀበልሽ ፈለቀ፣**
**ደግሞ ሌላ እሾህ ሌላ አጋም ፀደቀ።"**

ከገጣሚ ሄኖክ የሺጥላ "የሃበሻ ለቅሶ" ከተሰኘው ግጥም የተወሰደ



ኢትዮጵያን በአለም እንድትታወቅ ካደረጓት ነገሮች አንዱ የጥንታዊ የሰው ዘር መገኛ መሆኗ ነው።ለዚህ ደግሞ በአርኪዮሎጂ ቁፋሮ በፆታዋ ሴት የሆነችው ሉሲ መገኘት በቂ እማኝ ነው።አዎ!ሉሲ የኢትዮጵያ መገለጫ አርማ!!!

ግና....ዛሬ በጥንታዊቷ ሉሲ ሀገር ኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፍትህ ተነፍገው የፖለቲካ ተሳትፏቸውም ቢሆን እዚህ ግባ በማይባልበት ደረጃ ወደ ጥግ ተገፍትሮ በተወለዱበት ሀገር ህይወት ብርቱ ሰልፍ ሆናባቸው ለስደት፣ለሞትና እንግልት ሲዳረጉ እያየን ነው።ይህም በዋነኛነት የወያኔ መንግስት ፍሬ ቢስ ፖሊሲዎች ውጤት ሲሆን ይህንን ቀንበር በመስበር ፋና ወጊ ይሆናሉ ያሆናሉ ያልናቸው እህቶች ሳይቀር የዚህ አስከፊ ሥርዓት ሰለባ ሆነዋል።ለምሳሌ ጋዜጠኛ ሠርካለም ፋሲል ህጋዊ የሆነ ጋዜጣ አዘጋጅ በመሆኗና ሀሳቧን በነፃነት በመግለጿ ብቻ በግፍ ታስራና ህክምና ተከልክላ በወህኒ እንድትወልድ ስትገደድ፥የህግ ባለሙያዋ ክብርት ብርትኳን ሚደቅሳም "ይቅርታ አልጠየኩም" ብለሻል በሚል ተራ ንትርክ ምክንያት ከምትጦራቸው የ70 ዓመት አዛውንት እናቷና ከሷ ውጪ ሊንከባከባት የሚችል ከሌላት አንድ ህፃን ሴት ልጇ በመነጠል በእስር እንድትማቅቅ መደረጓ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው።በዚህም ሳይወሰን ሌላኛዋ እህታችን ጋዜጠኛ ርዕዮት አለሙ የጋዜጠኝነት ሙያዋን ተጠቅማ ስራዋን ስለሰራች ብቻ ዛሬም ድረስ በግፍ በወህኒ ተጥላ ትገኛለች።

በሌላ በኩል ይህ የመከነ የወያኔ ፖሊሲ በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለውን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ጫና መታደግ ባለመቻሉ ዛሬ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ሴቶች ድንበር አቋርጠው የሚሰደዱ ሲሆን በዚህም በብዛት በቀድሞ የወያኔ ወታደሮች በባለቤትነት የሚተዳደሩ "የጉዞ ወኪሎች" እህቶቻችንን ልክ እንደ ሸቀጥ በመሸጥ በደም የተነከረ ትርፍ በማጋበስ ላይ ይገኛሉ።

በቅርብ በወጡ መረጃዎች መሠረት የወያኔ አስተዳደር በአመት አርባ አምስት ሺህ ሴቶችን ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ለቤት ሠራተኛነት የሚልክ ሲሆን በዚህም ሴት እህቶቻችን ከአሠሪዎቻቸው በሚደርስባቸው ፆታዊ እና አካላዊ ጥቃት ምክንያት እየተሰቃዩ ይገኛል።

በመሆኑም እኛ ሴቶች የጉዳዩ ባለቤት እንደመሆናችን በሀገራችን ኢትዮጵያ የሴቶች ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እኩልነት የሚረጋገጥበት ፍትህዊ ሥርዓት ይገነባ ዘንድ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ላይ የምናደርገው አስተዋፆ ጎልቶ መውጣት ይኖርበታል፤ለዚህም ተሳትፏችንን አጠንክረን መቀጠል ይኖርብናል።በተባበረ ክንዳችን የጋራ ጥረት የሉሲ እምባ ይታበሳል!!!

# "ግመል ሰርቆ፥ማጎንበስ"

**Beyene Mesfin/Hof**

መቼም ግመልን ያህል ግዙፍ እና ረጅም እንስሳ ሰርቆ ግመሉን በማጎንበስ ከእይታ ለመሰወር መሞከር አንድም ድንቁርና




አልያም የለየለት እብደት ነው።
"የሙስና እናት" በመባል የምትታወቀው አዜብ መስፍንም ወያኔ/ኢህአዴግ ባደረገው ዘጠነኛ ድርጅታዊ ጉባኤ ላይ ስለ ሟቹ ባለቤቷ መለስ ዜናዊ ያደረገችው አሳፋሪ ንግግር ከማስገረሙም ባሻገር ስለሷ በሀፍረት እጃችንን በአፋችን ላይ እንድንጭን አድርጎናል።"በስድስት ሺህ ብር ደሞዝ በፔሮል በሚከፈል ክፍያ ብቻ በአለም ላይ የኖረው መለስ ብቻ ነው" ስትል የደፋር ድፍርስ አይኖቿን እያጉረጠረጠች ተናገረች።እሷስ ይህን ውሃ የማያነሳ ዲስኩር በቃላት ተናገረች፤እኔ ግን እላችኋለሁ፦በተጨባጭ ማስረጃ በማስደገፍ የስርዓቱ ቁንጮ የነበረው መለስ ዜናዊም ሆነ ባለቤቱ አዜብ መስፍን በሙስና የተጨማለቁ በአጠቃላይ ሥርዓቱም ቢሆን ሙስናን እንደ አንድ ህጋዊ
አሠራር በተግባር ተቀብሎ እየተጓዘ እንደሆነ ላሳይ እወዳለሁ።

"www.celebrities.com" የተሰኘው ድረ-ገጽ የታዋቂ ሰዎችን የንብረት መጠን መዝግቦ ይፋ የሚያወጣ ሲሆን በዚህ ድረ-ገጽ 'ሰርች ኢንጅን' /Search Engine/ ላይ መለስ ዜናዊ የሚለውን ስም ብታስገቡለት መለስ ዜናዊ በሩቅ ምስራቅ ሀገሮች በሚገኙ ባንኮች ውስጥ ያለው የገንዘብ ክምችት ሶስት ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር /$3,000,000,000.00/ እንደሆነ ይገልጻል።"ጉድ ነሽ!የአንኮበር ቅጠል" እንዲል የሀገሬ ሰው።ለመሆኑ ስድስት ሺህ ብር የወር ገቢ እየተገኘ በ21 ዓመት ውስጥ በየትኛው የአዜብ መስፍን ምትሃታዊ ቀመር ነው ሶስት ቢሊየን ዶላር ተቀማጭ ገንዘብ መሰብሰብ የሚቻለው?እኔ ግን እላለሁ፥መለስ ዜናዊም ሆነ ባለቤቱ አዜብ መስፍን እንዲሁም በአጠቃላይ የወያኔ ሥርዓት በዘረፋ የተሰማራ ሙስናም ልዩ መገለጫው ነው።

በሌላ በኩል የስፔን ጋዜጣ የሆነው ኤ.ቢ.ሲ ኢንተርናሽናል በ ጃንዋሪ 20, 2011 ቀን ባስቀመጠው ዘገባ አዜብ መስፍን በአንድ ቀን ብቻ በአውሮፓ ከተሞች በቻርተር አውሮፕላን እየተዘዋወረች በዲዛይነር ለተሰሩ አልባሳትና ውድ ጌጣጌጦች መግዣ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን ዩሮ /€1,200,000.00/ ወጪ ማድረጓን አስነብቦናል።ይህንንስ ከዛው ከስድስት ሺህ ብር ደሞዝ ላይ ነው ብለን እንመን?"ውሃን ምን ያስጮኸዋል?ቢሉ በውስጡ ያለው ድንጋይ" የሚባለው ተረት ካልሆነ በቀር የአዜብ "እኛ ንጹህ ነን" ምስክርነት እንዲሁ ግመል ሰርቆ ማጎንበስ አይነት ድንቁርና ይመስለኛል።

በአጠቃላይ በሀገራችን ለተንሰራፋው አስከፊ ድህነት እና ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍል የወያኔ ባለሥልጣናት ገደብ የለሽ በሙስና መዘፈቅ በዋናነት የሚጠቀስ ሲሆን ሥርዓቱ ያቋቋመው "ፀረ-ሙስና ኮሚሽን" የሚባለው መስሪያ ቤትም ቢሆን በእርግጥ ሙሰኞችን በማስረጃ በመያዝ ለፍርድ ቤት የሚያቀርብ ሳይሆን እነዚህ ሙሰኛ ባለስልጣናት ከስርዓቱ እንዳያፈነግጡ ለማስፈራራት ነገር ግን ካፈነገጡና የተለየ የፖለቲካ አቋም ከያዙ ብቻ በሙስና ወንጀል ከሶ ወህኒ ለማውረድ ወያኔ የሚጠቀምበት የፖለቲካ ዱላ ነው።

በመሆኑም ይህንን በሙስና የተጨማለቀ ሥርዓት ለማስወገድ ይልቁንም ተጠያቂነትና ፍትህ የሰፈነበትን የፖለቲካ ሥርዓት ለማስፈን በጋራ እንነሳ።

# ኢትዮጵያ መሪ እና ተቆርቋሪ የላትም

**Fissha Tsion Hailegeberile/ Kronach**

የተከበራችሁ አንባብያን እንደምናውቀው መሪ ማለት የሚመራ የሚያራምድ ከመጥፎ ነገር የሚሠውር ማለት ነው።ተቆርቋሪ ደግሞ ወገኑ ህዝቡ ሲራብ፣ሲጠማ የሚያዝን የሚቆረቆር ማለት ነው።ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆነና የወያኔ መንግስት ግን ህዝቡ በችግር ምክንያት እየተሠደደ በረሃ እና የእስር ቤት እንግልት ሲደርስበት አለሁ እንኳን አላለም።ያሳዝናል።ባለፈው በጅቡቲ በኩል ሀገር ለማቋረጥ በጀልባ ተጭነው ጀልባዋ በመገልበጧ ብዙ ወንድሞቻችን እና እህቶቻችን ኢትዮጵያውያን ከባህር ሰጥመዋል።

በኡጋንዳ በኩል ለማለፍ የሞከሩ ብዙ ወጣቶች ተይዘው በኮንቴይነር ተጭነው አየር በማጣታቸው ከሙቀቱ ግለት የተነሣ ብዙ ኢትዮጵያውያን ታፍነው አልቀዋል።በሊቢያ በኩል ለማለፍ የሞከሩ ኢትዮጵያውያን ከባህር ሰጥመው ቀርተዋል።ዛሬ የኬንያን እስር ቤቶች አጨናንቀው የሚገኙት የኢትዮጵያ ወጣቶች ናቸው።ታዲያ እነዚህ ውድ ወገኖቻችን በየጊዜው ሲያልቁ አለሁላችሁ የሚል አንድም የመንግስት አካል የለም።ታዲያ መሪ አለን?አዎ የሚያሳፍር መሪ አለን።የሚያሳፍር ተቆርቋሪ መንግስት አለን።እጅግ የሚያሳፍር ድርጊት በሳውዲ አረቢያ አንዲት ወጣት በኤንባሲው በር ላይ በፖሊሶች ስትደበደብ ተዋት ችግሯ ምንድነው ያለ የመንግስት አካል የለም።ታዲያ መሪ አለን ስንል ተቆርቋሪ አለን ስንል አያሳፍርም?እጅግ በጣም ያሳፍራል ኢትዮጵያ ግን የሚያሳፍራት አምላክ አላትና ሙስሊሙም ክርስቲያኑም አምላካችንን እንማፀን አበቃሁ።ቻዎ አምላካችን ከእፍረት ይሠውረን አሜን።

# በጨለማ ቤት ሠበራ

**Simret Ayalew Mengescha/ Höckstadt**

የተከበራችሁ ውድ አንባቢያን ምናልባት ለዛሬ የመረጥኩት ርዕስ ከሌላው ቀን ለየት ያለው ምክንያቱም ጨለማ እና ሰበራ ብዬ ርዕሴን ስጀምር ለምንድነው የሚለው ጥያቄ የሁላችንም ነው።አዎ በሁሉም ዘንድ ጥያቄ የሚያጭር ነው።እንደሚታወቀው ጨካኙ የወያኔ መንግስት በሀገራችን እየፈፀመ ያለው በደል እና አፈና እጅግ እየመረረ መጥቶአል።ለምን ቢባል መልሱ ለሁሉም ይከብዳል።

ተስማምቶ እና ተዋዶ የሚኖርን ህዝብ እርስ በርሶ ተለያይቶ ተጥላልቶ እንዲኖር አድርገው እንደገና ጥሮ ግሮ የሚኖርን ህዝብ ኑሮውን የሰቀቃ አድርጎታል።ዛሬ ዛሬ ደግሞ የወያኔ ወታደሮች በጨለማ ጭምብል ለብሰው የእያንዳንዱን ሙስሊም ቤት በአጥር እየዘለሉ በር በመስበር በመሳሪያ እያስፈራሩ ላፕ ቶፕ፣የሞባይል ቀፎዎች እንዲሁም ጠቃሚ ነገሮችን እየዘረፉ ናቸው።ነዋሪው ለምንድነው ብሎ ሲጠይቅ በዱላ ይደበደባሉ።የሚገርመው የአንድ ግለሠብ ቤት ያለፍርድ ቤት ማዘዣ ቤታቸው ተሠብሮ ቤታቸው እየተዘረፈ ነው ያለው ታዲያ አረመኔው የወያኔ መንግስት በጨለማ ቤት ሠበራውን በተደራጀ መልኩ እያካሄደው ስለሆነ ለወገን ለሀገራችን ህዝብ ጨለማውን ብርሃን እንዲያደርግላቸው አምላካችንን ወይም አላህን በጋራ እንለምን።አበቃሁ።


ተነስቷል!
He is Risen!
የማርቆስ ወንጌል 16:6
ethiopians.webs.com
መልካም የትንሳዔ በዓል
Happy Easter


ethiopians.webs.com
መልካም የትንሳዔ በዓል
Happy Easter

# The Dictatorial Government in Ethiopia and its Current Situation

**Amanuel Ogerasha, Abel/ Forchheim**

I felt strange in turn when I think about Ethiopian People's Revolutionary Democratic Front (EPRDF) or Tigray People's Liberation Front (TPLF) because, this ruling political parity in Ethiopia has been squashing the lives of Ethiopian citizens. Ethiopian people have been losing their life for many years and they are living in jail and suffer. God may give you the strength and hope! Ethiopian people are losing the title of human being by extreme control of TPLF as they have no power to do anything and still they are living without hope and moral. These tears of Ethiopian people do not remain as it! So may question is, how could this dictator TPLF hurts every time all Ethiopian in 21 century and who will care about for these mass of death and life's in prison? It is a fact that Ethiopian dictators posed a modicum of conundrum to anyone who studies the nature of their power. They believe any traditional categorization of regime type. On other hand, they style themselves as democratic and constitutional. They conduct elections, draft democratic constitutions, and establish "human rights" institutions, and tirelessly speak of the need for and their commitment to democracy. On other hand, they rib elections, embezzle public funds and intimidate, round up and torture and kill the opponent unconstrained by any notion of the rule of the rule law. Such governments strive to have it both ways at the same time: they wish to get the benefits of holding two apparently opponents' faces. The EPRDE has been akin to this type of rule, a master of this Janus-faced game (it isn't a game for the victims, of course). On its "democratic" face, it has deafened people with its rant of the need for the rule of law; ensured a more or less democratic constitution, conducted several elections, and installed a parliamentary system on its autocratic face, however, it defiled the constitutional system and the rule of law by violating the basic political and natural rights of citizens with impunity. By any standards, it has never been serving the law and the state. In fact, it has been the state and the law only for a benefit of this dictator ruling party in Ethiopia rather not for citizen. How have the two faces of the EPRDF gone alone together? They have been meant to deliver certain political functions internal and external to the state, and in principle, they are supposed to be exploited in their proper places, times, and context, and hence are not expected to be contradictory. But in practice, their relationship has usually been precarious or dangerously unstable.

Therefore, every Ethiopian must fight for freedom and stop activities of TPLF to set peace and stabilities in the country and now we must be totally engrossed in the life saving work by smashing the ways of our extreme enemy TPLF.

# Better to Starve...

**Weldekiros Asfaw/Bayreuth**

We can learn a lot from the following discusion of the Wolf and the Dog. It really shows us the relationship of Woyane/EPRDF members and the freedom fighters (seekers) of the entire Ethiopians.

A wolf that was almost Skin and bone -- because the dogs of the neighborhood guarded the sheep so well -- met a dog one night. The dog was as strong as he was fat. The wolf told the dog how good looking he was. The dog said, "It would be easy for you to get as fat as I am if you liked." "What would I have to do?" said the wolf. The dog said, "Almost nothing." They walked off together, but as they went along, the wolf noticed a bare spot on the dog's neck. "What is that mark?" said the wolf. "Oh, it is nothing," said the dog. "The collar that I wear when I'm tied up makes it." "Tied up!" cried the wolf, "tied up?" "Then you can't always run where you please?" "Well, not always," said the dog. "But what does that matter?" "It matters a lot to me," said the wolf, and turning away and ran back into the forest.

Better to starve and be free than to be fat and a slave to woyane/EPRDF!

# Still no change!

**Yostena Yelma Desalge/ Bayreuth**

TPLF is serving the same horrible wine in the same funny bottle that the people of Ethiopia are tired of. No real change has come to the table. Hailemariam Desalegn is a puppet, with no power base in the coalition.
Having been in power for the last 21 years, I wonder when the end of the road will come for this rotten regime. We are so sick of Woyanes. The TPLF regime is riddled with corruption and put Ethiopia among the UN list of 10 undeveloped countries in the world.

On the other hand, a few officials and some of the regime cronies are gathering unimaginable amount of wealth. Capital flight out of Ethiopia through corruption reached its all time high. People are unable to afford their daily bread. What are we waiting for before we the people of Ethiopia speak? This need to come to an end like Zenawi's life did.

# EPRDF: Inhuman regime!

**Kidest Zelalem/Köln**

It is absolutely unbelievable to hear that citizens are being uprooted or chased out from places they have been living, simply for having spoken a different language. In a country where, freedom, equality and democracy are preached, no one can believe this could happen. Some of us out of disbelief have been looking and searching for a justified explanation.We found none except believing that the government is perusing divide and rule policy that instigate enmity, hate and mistrust among people. What ever reason the government gives it is not reason at all and not convincing.

Most of us believed the incidence is not an isolated action it is a coordinated action. The action of the government is outright inhuman and a criminal act. EPRDF is failed and ashamed the Ethiopian people.

Here we are talking about the good economic achievements, the great dam, the promising future there we are ashamed to face the truth, what is really happening right now. I am really frustrated by everyday mismanagement, oppression, injustice and corruption. I used to convince myself by believing it is a transitional period. Such human right violation again and time again targeting a single group of people do not allow me to deceive myself any more. This time the oppositions have scored 100% for standing up for those victims of injustice. I am really sad, angry, and ashamed of EPRDF.

# Melese`s Fake legacy foundation!

**Bililigna Benber Aschager/ Bayreuth**

These days Woyane/EPRDF new song is Meles`s legacy foundation! I am sure this foundation is the place where his evil thought will be practiced and new evils will be fabricated for the beneficiaries of his family and loyalists, other wise it has nothing to do to Ethiopian people.

Just like EFFORT they will use it to suppress the people and magnify them selves. We heard that he and the family was living with 4000.00 birr ha ha ha...according to his mother of corruption wife. Except his worshippers and members of the evil party, we are not interested even to hear his name, let alone his legacy foundation etc. they can do what ever they like. Putting thousands in jail, displacing what ever they like, spending as much as they wish for any trash. His worshipers every time bore us saying he was smart, visionary etc...But practically we know that he was racist, dictator, evil and killer. So, for a leader who had such character what is the need to have foundation? This is a short question to Azeb and the so called PM Hailemariam! Or anyone who barks here and there like a dog, following them.




# Enough is enough!

**Elsa Hagos/Lahntal**

The TPLF/EPRDF regime in Ethiopia has been committing several crimes against the people of Ethiopia in the past many years. As it has been documented by several independent local & international organizations, The Ethiopian dictatorial regime inhuman ruling led to the death of many innocent people including children and women.

After the death of PM Meles Zenawi the Ethiopian people expects better ruling condition but the new PM Hailemariam Desalegne continues earlier plan and program that means EPRDF barbaric political program. And he can not to do something better or new. The new PM is under the control of EPRDF ruling classes (TPLF). He is both sides of a coin with Meles.

So, I call upon the entire Ethiopian people who are residing in Ethiopia and abroad to get rid of the dictatorial Woyane regime from our motherland .

# Anti-terrorism laws for other countries are security matters while for EPRDF it has become political

**Mekonen Taye/Forschheim**

It is reasonable to say that there is no conventional law worldwide concerning anti- terrorism. Having other country's anti terrorism laws under consideration we can say that Ethiopia's anti-terrorism laws are inconsistent with the constitution and other international human right laws. The anti-terrorism law which has been enacted in the country since 2009 possesses three major defectives. First, articles in the law open a wide door for interpretation. Second, most part of the law are in contrast with the supreme law of the country, The Constitution. And as a principle any law, rule or regulation inconsistent with the constitution is invalid which leaves the legality of the anti-terrorism law in question. The third and most basic problem of the law is that it is not clear which makes it even worse to abuse the intention of the law in the name of justice since any one can take his/her view of the law.

So the question would be what makes it so important to enact a law with this magnitude and inconsistent with the constitution. It is not because our country is a hot list in terrorist attacks - even some of the minor attacks

Ethiopia experienced were recently proved to be the plot of the government itself. Nor Ethiopia has any significant history to do with terrorism. The answer is somehow clear, first reason would be to warn and frighten those individuals and/or organizations who are struggling with the current regime on power. The victims of the law are likely to be Journalists, opposition parties and their members, civil servants and some NGO's working on human right issues etc. the law in a way prohibits or discourages those stake holders from acting or, the least, say anything on misappropriate handling of matters in every part of the country: - matters like administrative defectives, injustice acts and human right issues. The law wants these stake holders to remain silent while the government commits various minor and major crimes. The second reason is the political facts EPRDF (current regime) has at the moment. Obviously anti-terrorism laws for other countries are security matters while for EPRDF it has become political. This is evident when we look at the timing of the enactment of the law, i.e. just post of 2003 controversial national election when the regime was losing all grounds its credibility in the eyes of its nation and internationally. If we look at some of the articles in the law we can see how broad and ambiguous they are. Eg- Art652/2001 states "……. Blocking roads, possessing explosives and lighting………" but since making a peaceful demonstration even uses roads and as a result there will surely be some blocking of roads and any one can posses a match or liter but such things can be considered terrorist acts, according to the broad interpretation of the law. So the government can arrest and take any measure it thinks fit on any member of the participants.

The other example is that the constitution states under Art. 19 that any criminally suspected person should be arrested strictly after producing an arrest warrant and brought to court at least within 48 hours but contrary to this the anti terrorism law allows the police to detain a suspect for up to 4 months before any charges are made against the suspect. The law also permits police to conduct home search without producing any search warrant from the responsible authority, tab private phones, and check postal correspondences which are all invasion of privacy which is against the constitution.

Unlike same laws in Nigeria, Kenya or U.S.A making any kind of contact with a suspected terrorist regardless of the content of the message would amount to cooperating with a terrorist in our country. The U.S, being the most vulnerable and primary victim of terrorist attacks and having severe history with terrorism in the past 2 decades, has not enacted laws which are so rigid and wide for interpretation but on the other hand Ethiopia, with almost no history with terrorism, has such laws. The worst part of the law is that one can be in jailed for up to three years just because the government prosecutor thinks that the person has with hold information. When you see the severe punishment (25 years of imprisonment) one receives is he/ she makes any kind of contact with a suspected terrorist we can say that the true intention of the law is not rule of law but spilling deep fear on every person or organization who tries to do anything other than what the government says or do.

# Let`s Stop Harassment

**Zenebech Mamo/Fulda**

In order that the woyane regime to keep his advantage leading the people to death prison and migration to other countries.

The woyane regime is discriminating the Ethiopian people interms of humanity, excessive usage of the natural resource, holding back the people interests, and motivating the people to migrate to other countries.

Especially citizens who live on their own countries can not raise their rights & responsibilities. If they step forward the woyane regime justified in the name of terrorism and suffering them.

Woyane is destructing the country. One of the reasons is shortage of shelter, increasing the number of unemployment, poverty; deficiency of health and education policy and increasing of the migrant people is the destiny of the country. Currently in Ethiopia, human rights are highly violated by the woyane regime.

The woyane regime said that nation and nationalities have rights to decide on their rights, but none of each working. The people who rose about democratic rights are facing a lot of problems. Good examples of recent memories are Oromo, Amhara, Gedio, Agnwak, Sidama and Addis Ababa people leading them to death, prison and tortures under his feet by his hypocratic power.

In urban areas, farmers are loosing their land as of investors. This causes most farmers for being homeless, hunger and poverty. To avoid this discriminating powerof the woyane regime stand aside by the Ethiopian people`s patriotic front Guard today!

# Leave to live!

**Habtam Alemneh Belay/ Heusenstamm**

The corrupt dictatorial regime led by EPRDF, who has been in power for 21 years controls all the strategic income generating sectors such as agriculture, industry and Mining, is bitterly resented by the general populations that views it as a deliberate ethnic based systematic economic exploitation. As a ruling party, not only owns strategic sectors of the economy and engages in commercial and trading activities, but also uses its economic dominance as a political weapon to harass, incarcerate and dominate, weaken and control opposition forces in order to stay in power indefinitely.

Since March 2012, over a thousand

opposition party members, supporters and journalists have been arrested in Ethiopia for alleged involvement with various proscribed terrorist groups. By November last year, 207 of the detainees have been charged with crimes under the Anti Terrorism proclamation and the crime code. It is believed that the prolonged series of arrests and prosecutions indicated systematic use of the law and the pretext of counter- terrorism by the Ethiopian government to silence people who criticize or questions their action and policies which is a clear indication of an intensified crackdown on freedom of expression in Ethiopia.

That`s why:- most of us left our motherland to have a fresh air of real democracy. But we need to fight to assure our rights by any means. Long live to our struggle!!!

# Rope to tie a dictator!

**Yordanos Hailegiorgis/Lahntal**

It is indeed a colossal shame and gigantic disgrace when the tail is wagging the dog incessantly for twenty plus years. Now don't play the blame game again since the blame goes all around – just answer the clarion call and the tortured souls' cry and do the right thing!!! By any means necessary!!!

It is the crime syndicate in power, namely woyane, and their foreign collaborators who unfortunately set the agenda; and the rest of us slavishly take ethnic politics to heart and the ensuring hate as prescription drug and have been regurgitating for the last two decades. Can we look around where we stand in the world?

This shame has been deliberately brought upon us by neo-Banda leaders who hate greater Ethiopia and especially reserved inveterate hate against Amharas who have jealously guarded Ethiopia's territorial integrity throughout history.

Hello folks, can we forge ahead as a nation by tearing off the dirty ethnic cloth the woyanes are enveloping on our great nation and playing hate tune in our psyche? The rest of the world is taking upward spin leaving us in the dirt while this primitive form of ethnic politics is driving the country in a downward spiral. Two decades of slumber is unhealthy. Wake up Ethiopians!!!

# Let`s redeem our holy land Ethiopia!

**Elsa Diriba/Fulda**

One of the special things that make our country Ethiopia different from other continent and countries is that several ethnicities and ethnic group have about 80 different languages of their own and the most important thing also that all of these different ethnics groups have a believe for a motto that says ``one Ethiopia one country``.

But now a day, the regime of the woyane government is destroying this country which has lived for 3000 years as united, dividing them according to their own language and motivating them to leave alone.

If we go back to the past i.e 300 years ago, Ethiopia was living as united in peace eventhough there are variation in ethnicities, religion and language.

These divisions between ethnic group has been continued in creating conflicts between each other.and those who raise questions about their rights are led to prison and such a disastoures sufferings by the woyane regime and most of these victims are intellectuals and youths.

Because of all of these non democratic situations all over Ethiopia, people are accepting to have a hard life. That is why: most people are migrating to other countries.

Therefore, those who love your country`s unity not to be queit until the end of life. Instead you need to fight for your right with the cooperation of Ethiopian People`s Patriotic Front Guard (EPPFG). Long live Ethiopia!

# The Sufferings of the Helpless People

**Robel Dagne Weldegebrel/ Forchheim**

The primary role of a government is to serve and to take care of its own citizens. It includes protection of citizens from foreign enemies, providing justice & freedom to citizens and maintaining certain services. However, in contrary to this reality, the ruling Ethiopian People's Revolutionary Democratic Front / Tigray People's Liberation Front (EPRDF/ TPLF) has been oppressing its own people and commiting criminal acts against its own citizens to prolong its days in power. Ethnic based discriminations and violations have been the main criminal activities of the regime for the last two decades.

The ruling party, which is an ethnic based organization, has done lots of criminal acts to provoke ethnic conflicts among different ethnic groups of the country for the last twenty two years. In these years the Amhara people have been number one victims of the ruling party's deliberate and systematic killings and displacements. Recently, we have been hearing from local and international media and human rights organizations that thousands of ethnic Amhara's have been forcefully displaced from their homes and farmlands from western Ethiopia of Benshangun – gumz regional state. This is not the first time that the Amhara people displaced from their homes and farmlands in the last twenty one years. In the early and mid of 1990s hundreds of innocent Amhara people were deliberately killed and thousands were displaced from southern and south eastern parts of rural Ethiopia.

In the year 2012, it was also reported that more than 25,000 ethnic Amhara people had been forcefully displaced from their homes and farmlands in Guraferda woreda of southern Ethiopia regional state. According to some human rights advocates these displacements are illegal with respect to Ethiopia and international laws. Nevertheless, the displacements and the sufferings of the Amhara people have still been continuing in the above mentioned areas. For this reason this action should strongly and immediately be denounced.

All Ethiopians who live inside and outside of the country must oppose and denounce the recent mass displacements of the ethnic Amharas from different parts of the country and the human rights violations in Ethiopia. Moreover, the international human rights organizations should also give much emphasis for the situation and they should put pressures against the ruling party to stop its criminal acts against its own citizens. Unless what happens to the Amhara people doesn't stop immediately, we have to be sure that tomorrow it is going to happen to everyone and the miseries and the sufferings of the helpless people of Ethiopia is getting from bad to worse.

# Forced Evictions of Amhara shall not be solution for Ethnic Federalism

**Sisay Getachew/ Vlotho**

The Woyanne fascist junta is engaged in another ethnic cleansing campaign, this time in Benishangul Gumuz state against Amharas.

It is a shame to the Ethiopian authority to sit back and enjoy this misfortune. I am sure this eviction is encouraged by the government to force the Amharas to surrender to it's feet. The day will come the super rich and the corrupted Woyane leaders will pay for this immensely.

Why can`t we learn from our past mistakes. Haileselassie was overthrown because of the kingdom's corruption and greed. The cabinet and the riches were destroyed and punished.Megistu's government was overthrown because of it's corruption and non humanitarian act. They are still paying for it. And now Meles and his party is doing the same thing or worst to everyone in the 21st century.

History is repeating it's self and Africa is still backward. We have been insulted by everyone in the world including Arabs (who are still beating and killing our citizens in the Arab world). German Radio has reported last year, that 22,000 Amharas have been evicted from southern region`s Bench Maji Zone after their properties were confiscated.

So, we need to stand together to avoid this dictatorial and communist junta of the woyane regime by any means.



# We need not a personal rather a regime change!

**Ybekal Engeda Tsegaye/ Kassel**

As everybody knows after the death of the prime minister of Ethiopia Meles Zenawi, we expected a new dimensional change but the new prime minister has told us that there will never ever changes at all. So, we should have to continue our struggle until the change of EPRDF regime.

To assure an overall change in Ethiopia, we need to support every struggles of the entire community.

Then, as yesterdays we need to unite together and established a new peaceful, democratic, and developed Ethiopia. I call upon the whole Ethiopians to fulfill their responsibilities. May God bless Ethiopia!!!

# How long being Ignorant?

**Habtamu Tesfaye/Fulda**

The woyane regime who said that I am standing for democracy and but none of each working, is getting worse and worse in its discrimination power.

Recently, due to this discrimination, we are seeing so many problems happening in our country. The countrie`s political and economic problem has caused people to migrate to different other countries and live as a refugee, and so many our sisters and brothers are obliged to live as slaves in different Arabian countries. The refugees are losing their lives during

migration upon the desert & oceans during their journey too.

The division of different ethnic groups has caused people to a lot of individualism and hatred causing a problem upon the unity of the country.such examples are Borena up on Konso,Guji upon Gedio as well as Gambela. In rural areas, farmers are also loosing their land as of investors. Many ancient churchs which are above 1500 years old and historical places are also getting destroyed as for building factories. People are not united instead they are subject to division and hatred each other.

Therefore, my country people our country which has tremendous history more than 3000 years is getting destructed and its culture and development is declining due to segregation.

From the people of Ethiopia more than half of them are the Oromo people.these people are also facing a great problem like most other peoples. Therefore, is our ignorance not enough?

Are we waiting to see our country led into such a horrible situation like Rwanda as s result of that devastating civil war? And we say and make a call who ever love his country who ever has a long thirst to see his free country

Let him stand aside by the side of Oromo Libration Front (OLF) who is fighting for his freedom and to eliminate the dictator Woyane regime. Victory to the people of Oromo!

# Thanks ESAT TV and Radio!

**Debebe Kebede/Goch**

The action of evicting and deporting ethnic Amaharas from the Benishangul-Gumuz ethnic state in western Ethiopia is a horrific crime and a crime against humanity by any measure and the outrage of Ethiopians across the world is justified.
The stories we hear from the victims themselves and the witnesses who saw it are heart wrenching. Thanks to social media and communication technology, we are hearing from the victims themselves and seeing some of their tragic pictures in real time irrespective of where we live. Thanks to the folks at ESAT TV and Radio for the relentless coverage.

I have even heard many supporters of the Ethiopian regime, at least those who live outside of Ethiopia, condemn this barbarism. They should be applauded for that. What kind of sane person cannot be outraged when watching this replay of a Nazi pogrom that targets an ethnic group who were literally frog-marched and, in the words of the victims themselves, told to go to “their country” and “wherever their ancestors were born”? What do you feel when you are told this nonsense in your own country, the country your fathers and forefathers defended and died for?this is simply remarkable shame!

The victimized ethnic Amharas were beaten, violently dragged off their homes and forced to pay for the trucks that packed them inhumanely, transported them out of the Benishangul Gumuz state, and dump them at the edge of another ethnic homeland without anything to help them stay even for a day. The government has not even denied or confirmed reports that one truck loaded with more than sixty people had overturned at night and fifty nine deportees were killed. We heard that women were giving birth in the wilderness and children died of suffocation. What kind of decent human being would watch this unconscionable action of a government do this to its own people, particularly to the most vulnerable and not get outraged?
So, what are we waiting for? The Today`s incident against Amharas will going to other nations too in the near future. Therefore, we all Ethiopians, who are beleiving in united Ethiopia should have to stand together to avoid this Insane regime from our motherland!!!



# Anti-Religious Freedom in Ethiopia

**Hilina Dawit/Nürnberg**

The Ethiopian constitution, adopted in 1994, formally separates church and state and guarantees freedom of religion for Ethiopian citizens. The separation of church and state is enforced in both the public and private

spheres; religious instruction is restricted to mosques and churches and is explicitly banned in both public and private schools.

But recently, Human Right groups expressed grave concern over official encroachments on religious freedom in Ethiopia. I lamented the fact that religious freedom was becoming a new focal target of official human rights violations. But I was also encouraged by the steadfast resistance of some principled Christian and Muslim religious leaders to official interference in religious affairs. I noted that “For the past two decades, Ethiopia has been the scene of crimes against humanity and crimes against nature.

Officials of the ruling regime in Ethiopia see the issue of religious freedom as a problem of “religious extremism”. The late Meles Zenawi alleged that some Christians at the Timket celebrations (baptism of Jesus, epiphany) earlier this year had carried signs and slogans expressing their desire to have a “Christian government in Ethiopia”. He also leveled similar accusations against some Ethiopian Muslims protesting official interference in their religious affairs for being “Salafis” linked to Al Qaeda. Meles claimed that “for the first time, an Al Qaeda cell has been found in Ethiopia. Most of them, in Bale and Arsi``, said Meles.

Following this unreal generalization, Ethiopian religious leaders say Ethiopia is the scene of crimes against divinity. So, to assure our freedom of religion, we Christian and Muslim leaders and followers should have to continue the struggle against the dictatorial regime of Woyane.

# The Mere Solution

**Dian Teka Teshome/Bayreuth**

We were hoping that the death of the dictator Zenawi would bring some change in Ethiopia. But practically we have seen that the situation is worsening and worsening in the course of time. Arbitrary arrest of citizens, repression of freedom of expression, corruption, arrest of journalists and opposition party leaders, expulsion of one ethnic group from different parts of the country are increasing in their magnitude.

So, unless there is a total change of regime in Ethiopia there will never be a hope for democracy, freedom and equality. We must fight TPLF until we ensure our political and civic rights and then establish an empowered civic society.

# አፓርታይዳዊው የወያኔ ሥርዓት ሊወገድ ይገባል

**Abel Tesfa/Hof**

የወያኔ አስተዳደር ገና ከጅምሩ ራሱን የአንድ አካባቢ ነጻ አውጪ አድርጎ የተንቀሳቀሰ ሲሆን እነሆ ዛሬም ድረስ ይህን ስያሜውን ለመቀየር እንኳን ፍላጎት ያላሳየ ይልቁንም ቀሪ የሀገሪቱን ህዝቦች በዘር መስመር በመከፋፈል ልክ እንደቀድሞው የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ አስተዳደር በእያንዳንዱ ዜጋ የመታወቂያ ካርድ ላይ ብሔሩን በመፃፍ፣ታሪካዊ ኩነቶችን አጋኖ በማቅረብ በዚህም ዜጎች አንዱ የአንዱ ታሪካዊ ጠላት ሆኖ እንዲተያይ በማድረግ፣የተወሰኑ ቁልፍ የስልጣን ቦታዎችን በተለየ ሁኔታ ከአንድ አካባቢ ለመጡ ሰዎች ብቻ እንዲሰጥ በማድረግ፣ዜጎች በሀገሪቱ የትኛውም ክፍል ያለገደብ ተዘዋውረው እንዳይሰሩ በህቡዕ በመከልከል፣ የተወሰኑ የስርዓቱ ተቃዋሚዎችን በዘር መስመራቸው ምክንያት ብቻ ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና እንዲደርስባቸው በማድረግ፣የሀገሪቱን ሀብት በጥቂት የስርዓቱ ደጋፊዎች ቁጥጥር ስር በማድረግ አፓርታይዳዊ ሥርዓቱን ከገነባ እነሆ ድፍን ሃያ ሁለት ዓመታት ተቆጠሩ።

በሀገራችን እየታየ ያለው ሁኔታ በዚሁ እንዲቀጥል ከፈቀድን ከዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ፍፁም ባፈነገጠ መልኩ "ከብዙኃን አስተዳደርና የአናሳዎች መብት" ይልቅ አሁን እየታየ እንዳለው የአናሳዎች አስተዳደርና የብዙኃን ከባርነት ያልተናነሰ ተገዢነት ሙሉ በሙሉ እንደሚሰፍን ምንም አያጠያይቅም።

ስለሆነም በወያኔ ላይ የምናደርገው ትግል ነገ እንደሰው የምንኖርበትን አልያም በባርነት ለዘመናት የምንቀጥልበትን ቁልፍ ጥያቄ የሚመልስ ሆኖ እናገኘዋለን።ለዚህ የህልውናችን የመሰረት ድንጋይ ለሆነ ትግል የጋራ ጥረት እና ህብረት ያስፈልገናል።

በተባበረ ክንዳችን የባርነት ቀንበር ይሰበራል፥በአላማ ፅናታችን የዴሞክራሲ ጮራ በኢትዮጵያ ይፈነጥቃል!!!

## ይሁዳ ሲፈጠር

አስራደው /ከፈረንሳይ

አምላክ እያወቀ ይሁዳን ሲፈጥረው
ልጁን ኢየሱስን ነበር እንዲሸጠው
ባይወለድ እማ ይሁዳ በዚች ምድር
ለክርስቶስ መሞት ማን ምክንያት ነበር?
ያዳምስ ሃጢያቱ መች ይሰረይ ነበር?!

በገባለት ቃሉ አዳምን ለማዳን
እንዲሸጠው ልጁን ፈጠረ ይሁዳን
ይሁዳን ባይፈጥር ባምላክነት እጁ
አብን በቸገረው እንዲሰቀል ልጁ።
በመስቀል ተሰቅሎ ክርስቶስ እንዲሞት
ይሁዳ ኢየሱስን መሳም ነበረበት
መሳም ያለየለት ውሉ የጠፋበት
ጥላቻና ፍቅር ተደባልቀውበት።

ባይሸጥማ ኖሮ ይሁዳ ኢየሱስን በጥቂት ጭብጥ ብር
ኢየሱስን ኢየሱስ ይሁዳን ይሁዳ
ባላልናቸው ነበር።

መልካም የትንሳኤ በዓል ለሁላችን
ሚያዝያ 27/2005 ዓ.ም
ጥላ መጽሔት

# Deutsch vs Deutsch Champions league Finale !




## ለ90 ደቂቃ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ለመክፈል አልመዋል ወይስ......?

አንዳንድ ሰዎች ማንም ቅሪላውን ለተላፋው እናንተ የምን ቤት ናችሁ?”ከድር ሊያገባ ነስሮ ወጣ ገባ” በማለት የደጋፊዎችን ልባዊ የኳስ ፍቅር ለማጣጣል ሲሞክሩ ይስተዋላሉ።እግር ኳስ የዓለም ቋንቋ መሆኑን የዘነጉትን ሰዎች ዛሬ ደግሞ ከመቀመጫቸው የሚያዘልላቸው እውነት ልንነግራቸው እንገደዳለን።አንዳንዶቻችሁ ቅሪላ ለምትሏት ኳስ ሲያውም ለ90 ደቂቃ ብቻ አሁን አንድ ሚሊዮን ሃያ አምስት ሺ ብር ካልከፈሉ ስታዲየም ተገኝተው ማየት አይፈቀድሎትም ቢባሉ ምን ይላሉ?

እ.አ.አ የፊታችን ሜይ 25/2013 ለንደን ዌምብሌይ ስታዲየም ለሚከናወነው የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ የዋንጫ ግጥሚያ በ“VIP“ ማዕረግ ግጥሚያውን ለመከታተል ለሚሹ 41ሺ336 ዩሮ መክፈል ግድ ይላቸዋል።በአገራችን አጠራር ሚስማር ተራ እንደሚባለው ከሆነ ደግሞ በትንሹ 2ሺ ዩሮ ወይም 50 ሺ ብር መክፈል ይጠበቅቦታል።ስለተከፈለባት ብቻ እንኳን ኳስ ኳስ እንጂ ቅሪላ አለመሆኗን ልብ ይሏል።

በአውሮፓ ምድር ከባርሴሎናው ካምፕ ኑ ቀጥሎ በግዝፈቱ ወደር ያልተገኘለት የ133 ሜትር ቁመት ያለው የለንደኑ ዌምብሌይ ስታዲየም 90 ሺ ተመልካቾችን የማስተናገድ አቅም አለው።በዚህ ግጥሚያ ስታዲየሙ  በትንሹ ከትኬት ሽያጩ ብቻ 2 ቢሊዮን ዩሮ ወይም 50 ቢሊዮን የሚጠጋ ብር ይገኝበታል።ሌሎች ሽያጮችን አለማካተታችንን መቼም አንባብያን እንደሚያጤኑልን እንገነዘባለን።አንድ ዓለም አቀፍ ስታዲየም ገንብቼ በአንድ ዓመት ወጪዬን ልሸፍን የሚል  ባለሃብት ጉዳዩን ቢያስብበት ሳያዋጣ ይቀራል ብላችሁ ነው?የነዳጅ ብር ያጠገባቸው አንዳንድ የዓረቡ ዓለም ባለሃብቶች አንድ ቀን ነዳጁ ቢነጥፍስ ብለው ይሁን ወይም ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ምንም እንኳን ስለኳስ ባያውቁም የአውሮፓ ክለቦችን የግል ንብረታቸው ማድረጉን እያቀላጠፉት ነው።

ታዋቂው የደቡብ አፍሪካ የመጀመሪያው ጥቁር ፕሬዚዳንት ኔልሰን ማንዴላ ስፖርትን አስመልክተው እንደተናገሩት ኳስ ማለት ስፖርት ስፖርት ማለት ኳስ መሆኑን ቅሪላ አድናቂዎች ለሚሉን ተከታዩን ምርጥ አፍሪካዊና አባታዊ ጥቅስ እንዲያነቡ እንጋብዛለን።**“Sport has the power to change the world. it has the power to unite in a way that little else does. it speaks to youth in a language that they understand. Sport can create hope where there once was only despair. It`s ore powerful than governments in breaking down racial barriers. It laughs in the face of all types of  discrimination.”**- NELSON MANDELA

ጀርመኖቹ ስፔኖቹን አንገት አስደፍተው በኳስ ቋንቋ ቀጥቅጠው በዝረራ ከውድድሩ ካሰናበቷቸው በሁዋላ ባየር ሙንሽን(ሙኒክ) እና ቦሪሲያ ዶርትሙንድ ለዘንድሮው የአውሮፓ ቻምፒየንስ ሊግ የፍፃሜ ግጥሚያ ደርሰዋል።ውጤቱን ማንም ያልገመተውና ያልጠበቀው በመሆኑም ወይ ኳስ አንቺ ድቡልቡል ከማለት ውጭ ሌላ አባባል ለጊዜው አልመጣልንም።

ታዲያ የማህበራዊ ድረ-ገፆችን ያጣበበው ይኸው ርዕስ ውድድሩ እስከሚያልቅም እንዲሁ ይቀጥላል።እዚህ ጀርመን ውስጥ የሁለቱ ክለቦች ደጋፊዎችና ሚዲያው የጦፈ ክርክር እያደረጉ ናቸው።ሁለቱ የጀርመን ቡድኖች ለዋንጫ ያለፉት የአገሪቱ ቡንደስ ሊጋ ከእንግሊዙ ፕሪሚየር ሊግ ወይም ከስፔኑ ላሊጋ ስለበለጠ ወይስ በእድል? ከፍተኛ ሙግት ገጥመዋል ጀርመኖቹ።  አንድ እውነት ግን አለ ባርሳን የሚያህል ታላቅ ክለብ በደርሶ መልስ 7ለ0 ማሸነፍ ዕድል ነውን? አይመስለንም።ቡንደስ ሊጋው በለጠ እንዳንልም ከነዚሁ ከሁለቱ ክለቦች የተሻለ ቡድን በባትሪ አይደለም በፀሓይም ቢፈልጉ አያገኙም።እና ምንድን ነው? መልሱን ለእናንተ ትተነዋል። በቂ ገንዘብ ለሌለን የፍፃሜ ግጥሚያውን የየአገራችን ቴሌቪዥን ጣቢያዎች በነፃ ያስተላልፉልናልና በያለንበት እንዝናና ኳስ የዓለም ቋንቋ ነውና።በኢትዮጵያ የቀንና የዓመት ስሌት ቅዳሜ ግንቦት 17/2005 ዓ.ም ከምሽቱ 2 ሰዓት ከ45 ለንደን ዌምብሌይ ላይ እንገናኝ።ቸር እንሰንብት!




# ጥላ መጽሔት ሰባተኛ እትም

**ጥላ መጽሔት 2ኛ ዓመት ሰባተኛ እትሟን ይዛ July 31/2013 ለንባብ ትበቃለች። ስለዚህ አዲስና ነባር ደንበኞቻችን በተለመደው አድራሻችን ታገኙናላችሁ። በመጽሔታችን ላይ ያላችሁን አስተያየትና መልዕክቶች ሁሉ እስከ July25/2013 ድረስ ልታደርሱን ትችላላችሁ።**

**ለበለጠ መረጃ የስልክ መስመራችንን መጠቀም ይቻላል።**

**WIR SIND IMMER FÜR SIE DA!**

**አድራሻችን**
**Mesfin Abraha**
**Löhrgasse 4**
**36251 Bad Hersfeld**
**E-Mail: tilamagazine@yahoo.de**
**Web-Site: tilamagazine.yolasite.com**
**Tel.No. 0152- 22195567**
**0176- 59384456**
**0176- 68830082, 0176-71668780**

**TILA MAGAZIN IST EURE MAGAZIN**